# መለኮት ሲብራራ

እናመሰግናለን፡ ወንድም ካርልሰን። ጌታን የምታገለግሉ ወንድሞች እና እህቶች በሙሉ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። አንዳንዴ... ዛሬ ጠዋት ሳደርግ እንደነበር፡ እንዲህ ያሉ ቆንጆ ምስክርነቶች፡ እና ሌላ ሌላ ነገሮች ማዳመጥ ከጀመርኩ፡ ቶሎ መነሳት ይከብደኛል። እንዲሁም፡ ወንድማችን እና እህታችን እንዳሳለፉት መከራ እና ሰደት፡ እኔም አብሬአቸው አልፌበታለሁና፡ ቀደም ሲል—እኔም ራሴ፡ ከባፕቲስት፡ የባፕቲስት ሚሺነሪ የነበርኩ ስለሆነ—ከወገኖች እንዲህ ሲደርስብህ ምን ማለት እንደሆነ ይገባኛል...

2 እኔም ተመሳሳይ ነገር ገጥሞኛልና። የገዛ ወገኖቼ ተነስተውብኝ፡ አብደዋል ብለው ሰላሰቡኝ እኔን ማሳደድ የሚችሉ መሰሏቸው ነበር። እኔም ስለገባኝ፡ ብዙ ጊዜ በሰምና ወርቅ መልስ እሰጥበታለሁ፡ "አብደዋል ካላችሁኝ፡ ጤነኛ ከነበርኩበት ዘመን ይልቅ፡ ካበድኩ በኋላ ደስተኛ ሆኛለሁና፡ ተውኝ።" ለራሴም የያዝኩት፡ ፍልስፍና ይህ ነው። በርግጥም—በዚህ ጊዜ እንዲህ በመሆኔ—እጅግ ተባርኬበታለሁ።

3 እዚህ ያለችው የወንድማችን፡ ትንሿ ቸርች ኦፍ ክራይስት፡ በተለምዶ ካምቤላይት ብለን እንጠራታለን። ስንጀምር አካባቢ የሰብሰባዎቻችን ቀንደኛ ጠላቶች እንደነበሩ በትክክል አስታውሳለሁ። እንደምታውቁት፡ ፖል የተባለ አንድ ሰውም ይህ ነገር ገጥሞት ያውቃል፡ ከዛ በኋላ ግን ከእኛ እንደ አንድ ሆነ። ስለዚህ፡ ይህ ነገር እውነት ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚፈልጉት ህይወታችሁ ነው። ታውቃላችሁ፡ ስብከት ከምትሰብኩኝ፡ ህይወታችሁ ይሻለኛል፡ ሁልጊዜ። እንደው...

4 አንድ ጊዜ፡ አንድ ታላቅ አገልጋይ፡ ጥሩ የሙሉ-ወንጌል ሰው፡ ሬቨረንድ ቡዝ-ክሊቦርን፡ ይባላል፡ ሁላችሁም—ታውቁታላችሁ፡ በተለያዩ ሰባት ቋንቋዎች ወንጌልን ይሰብካል። አዋቂ ሰው ነው። ባለ ግዙፍ አእምሮ ነው፡ ከኔ ጋር... እኔ እሱና ወንድም ሞር፡ አብረን ከኔ ጋር እየሄድን፡ ስለ አንድ ርዕሰ እየተወያየን እንሄድን ነበር። እና እኔ ከሒሳቡ ተቃራኒ ሆንኩበትና፡ ዞር ብሎ አየኝ። "መጽሐፍ ቅዱስህን'ኳን አታውቀውም፡" አለኝ። ወንድም ቡዝ እንዴት እንደሚናገር ታውቁታላችሁ።

5 እኔም "እውነት ነው፡ ወንድም ቡዝ፡ ግን ደራሲውን በደንብ አውቀዋለሁ፡" አልኩት። ስለዚህ፡ እኔ—ፍላጎቴ... ታውቃላችሁ፡ "እርሱን ማወቅ እንጂ፡" ቃሉን ማወቅ፡ ሕይወት አይደለም፡ ይሄን እወቁ። አያችሁ? ቃሉን ባላውቅም፡ ብቻ እርሱን ልወቀው! ይህ እውነት ነው።

6 ዛሬ ጠዋት፡ ከዚህ ጥሩ ህብረት ጋር፡ ከአገልጋዮችም ጋር፡ እጅ እየተጨባበጥኩ ነበር። እና እዚያ ጋር ቁጭ እንዳልኩ እንዲህ ሆነ... ማንንም ሰው ለማጋለጥ ፈልጌ አይደለሁም። ነገር ግን እዚህ ጋር ያለው፡ ይህ ጥቁር ወንድም መጣና፡ ቁጭ አለ። እኔም ለጸሐፊዬ፡ "ይህ ሰው እውነተኛ ክርስትያን ነው፡" አልኩት።

7 በኢን ክራይስት ቸርች ኦፍ ጋድ የነበረው ሽማግሌ ሰሚዝን አስታውሰከኝ፡ መሰለኝ። እዛ እየሄድኩ በተደጋጋሚ እሰብካቸው ነበር፡ እና—አሁንም ይታየኛል። በመጠኑም ይህ ወንድምን ይመስላል፡ ብቻ እሱ የተወሰነ ሰርገኛ ፂም ነበረው። በኋላ በር በኩል እገባ ነበርና፡ ሽማግሌው የሚናገረውን ፈጽሞ አልረሳውም፤ እያቸዋለሁ፡ ቅዱሳኖች ሁሉ፡ መዝሙር እየዘመሩ፡ ሌላ ደግሞ፡ ጥግ ላይ የምትቀመጥ፡ እንዲት ትንሽ ልጅ ነበረች። በጣም የምወደው ዝማሬ **ሊፍት ሂም አፕ** ነበር። ሁሉንም፡ **ሊፍት ሂም አፕ** እየዘመሩ፡ በጴንጤቆሰጤ መንገድ፡ ያጨበጭባሉ። ይወዱኛል፡ እኔም እወዳቸዋለሁ። ወደ ውስጥ ስንገባ (እሱ እዚያ ላይ ተቀምጦ፣ ጭንቅላቱን **እንዲህ** አድርጎ፡ ጠረጴዛው ላይ፡ ዝም ብሎ ይመለከታቸዋል፡ ታውቃላችሁ።)፡ "ግባ፡ ሽማግሌው። ቆብህን አሳርፍ።" ይለኛል እንጂ፡ "ኖር አይለኝም።" "ቆብህን አሳርፍ፡" ይለኛል።

8 ያኔ፡ ያወቅኩት፡ ይህ ወንድም፡ ሚሰቱ እጅግ ከምወዳቸው የወንግጌል ዘማሪዎች አንዷ ናት። እሷ እንድትዘምር ፈልጌ፡ የምችለውን ያክል መዝሙሩን ነካ ነካ አደርገው ነበር። ያኔ፡ አድርጊ ተብላ እንድትጠራ አትወድም ነበር፡ ይህም፡ እኔ ራሴ ምን ማለት እንደሆነ ይገባኛል። ከቻለች ግን፡ መጥታ እንድትዘምር፡ እኔ በግሌ እጋብዛታለሁ።

9 ቆይ፡ አንቺ እህት—በክርሰትያን ቢዝነስ ሜን፡ **ሺፕ አሆይ**፡ የሚለውን መዝሙር የዘመርሽው እህት፡ አይደለሽም እንዴ? [እሷም "አዎን፡ ጌታዬ፡ አዎን።" አለች።—አርታዒ።] ባለቤቴ በዚህ ሳምንት ትመጣለች ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ ሰትዘምሪ እንድትሰማሽ እፈልጋለሁ፡ በጣም አካብጄባታላሁና። መዝሙሩን ቴፕ ውሰጥ ካጣችሁት፡ እኛ እናሰተካክላለን። መዝሙሩን እወደዋለሁ።

10 እኔም፡ ወገኖችን፡ መዘመር እንደማልችል—እነግራቸው ነበር። ኦህ፡ ማይ፡ ሚልዮን ማይልሰ የማይችል ሰው ነበርኩና። ነገር ግን እላችኋለሁ፦ "ወደ መንግሰተ ሰማያት ገብታችሁ፡ እንደው፡ እዛው፡ በትልቁ ቤተ መንግሰት ሰትኖሩ፡" እላችኋለሁ፡ "ከኮረብታው ግርጌ ወደ ታች፡ ጥግ ላይ ባለው ጫካ ውሰጥ፡ እዚያ ማዶ አንድ ትንሽ ጎጆ ትገኛላችና። እሷ የኔ ናት። ምናልባት አንድ ቀን ማለዳ ወደ ደጃፍ ወጥታችሁ አንድ ሰው በዚያ ቆሞ፡ 'አሜዚንግ ግሬስ! ሃው ሰዊት ዘ ሳውንድ፡ ሴቭድ ኤ ሬች ላይክ ሚ!' ሲዘምር ከሰማችሁት፡ 'እግዚአብሔር ይመሰገን! ወንድም ብራንሃም በሰተመጨረሻ መዘመር ቻለ፡'" በሉ። እዚያ ማዶ፡ ሲዘምር የምትሰሙት ሰው እኔው ነኝ።

11 ለክርሰቲያን ወንድሞቼ፡ እና… ዛሬ ጠዋት፡ አንድ ወንድም የቡድሃ አገልጋይ ነው ብሎ፡ እዚህጋ፡ ሰው ያሰተዋወቀን መሰለኝ። ለአንተም ሰላምታዬ ይድረሰህ፡ ወድ ወዳጄ። ብዙ ባይሆንም፡ ከቡድሃ ተከታዮች ጋር፡ በተወሰነ መልኩ ግኑኝነት ነበረኝ፤ በተለይ ደግሞ በካናዳ ያሉ፡ ቻይናውያን መካከል ውሰጥ፡ እጅግ መልካሞች ደጋጎች ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

12 አንድ የቡድሃ ተከታይ ሰው ከቡድሃ ቴምፕል፡ ዊንግፔግ ወደ ነበረ ጉባኤ ሲመጣ አሰታውሳለሁ፡ አይነ ሰውር ነበረ። አጫጭር፡ እና ደጋግ ትንንሽ ሰዎች ናቸው፡ እግዚአብሔር ፈዋሽ እንደሆነም ያምኑ ነበር። እኔ ለሱ በምጸልይበት ጊዜ፡ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚወድ፡ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡ ዓይኖቹም

ወዲያው ተከፈቱ፡ በዚያም… እንዲህ መሆኑ—ድንቅ ነገር ሆነ። ስለዚህ፡ ሰውን ሁሉ—እናንተንም ሁላችሁ እናመሰግናችኋለን።

13 ከዚህ በፊት፡ በቺካጎ፡ ለመናገር፡ እድል አላገኘሁም ነበር… ምንም ቢሆን፡ ምንም አይነት መልዕክት አመጣለሁ ብዬ አልሞክርም፡ እዚህ ያሉ አገልጋዮች፡ መልዕክት በማምጣት ከእኔ የተሻሉ ናቸውና። ከዚህ ሁሉ በላይ፡ ግን፡ መልዕክት ለመስማት እዚህ አልመጣችሁምና። ነገር ግን የቺካጎን፡ የዚህ ወረዳ አገልጋዮችን ለማግኘት እና ከእነርሱ ጋር በበለጠ ለመተዋወቅ፡ አንዳችን ከሌላው ለመተዋወቅ የምንችልበት፡ በጣም አስደሳች ጊዜ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰቤ ነበር። በርግጥ ደግሞ ስለዚህ ዕድልም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ምክንያቱ፡ በአንድ የቤተክርስቲያን ስፖንሰር እና፡ በክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ስፖንሰር ስር፡ ወደዚህ ከተማ በተደጋጋሚ መጥቻለሁ። በዚህም ምክንያት፡ ለወንድማማች ማሕበር ራሴን የማስተዋወቅ ዕድል አላገኘሁም።

14 እና—እንዲህ አይነት አገልግሎት፡ ሁልጊዜ የሚከተለው ነገር እንዳለ አስብኩ፡ አንዳንዴ ሰው በቀላሉ በተሳሳተ መንገድ እስኪረዳችሁ ድረስ፡ ውጣ ውረዶች፡ እና መውረድ እና መውጣቶች አሉ። ስለዚህ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ለወንድሞቼ—የቻልኩትን ያክል ግልጽ አድርጌ፡ በግልጽ ማብራራት እፈልጋለሁ።

15 እኔ—እንዲህ አይነት ሰንሴቲቭ ነገሮች በተማሩ ሰዎች ፊት ንግግር—ለማድረግ ብቃት እና ችሎታ ያለው ሰው አይደለሁም። ትምህርት የለኝም፡ ያ ይጎድለኛል። ጌታን ግን… እወደዋለሁ። ጌታም፡ ነፍሳትን የምማርክበት ሌላ መንገድ፡ ሰጥቶኛል፡ ወላጆቼ ሊሰጡኝ ያልቻሉትን፡ የትምህርት ክፍተት ይሞላ ዘንድ፡ መለኮታዊ ስጦታ ሰጥቶኛልና። አስር ልጆች፡ እና የታመመ አባት ባለበት፡ በድሃ ቤተሰብ ስለነበርኩ፡ የመማር እድል አላገኘሁም። ስለዚህ፡ ግን፡ እኔ ስወለድ፡ በአባቴ እና በእናቴ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተከሰተ… የሆነ ነገር ነበረ። የእኔን ታሪክ አንብባችኋልና። በዚህ ረገድም፡ ከእናንተ ከወንድሞቼ ጋር፡ ሐጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ ለማቅረብ፡ የራሴን ድርሻ ለመወጣት ሞክሬአለሁ። አሁንም…

16 አጉል እምነት የለኝም። ቃሉን ከመክፈቴ በፊት ግን፡ ሁል ጊዜ፡ ደራሲውን በጥቂቱ ማመጋገር እወዳለሁ። እስኪ ለአፍታ ያህል ራሶቻችንን ዝቅ ማድረግ ከቻልን ባካችሁ።

17 ውድ አባታችን ሆይ፡ አንተ አምላካችን ነህ፡ እኛም ስለ ወንጌል አንተን እንማጸንሃለን። በልጆችህ፡ በመጋቢዎችህ፡ እና በተወደደው እምነት ወንድማማቾች በሆኑ ሰዎች ፊት ተገኝቻለሁ። ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ተረድተዋቸው፡ ወደ ተቋማት በተላኩ በእነዚህ ፊት ተገኝቼ ስለ እግዚአብሔር መንግስት፡ በመጨረሻው ዘመን ልጆችህን እንዴት እንደምትጠራ በማየቴ እና በመስማቴ፡ ልቤን ደስ አሰኝቶኛል።

18 አባት ሆይ፡ በዘመን ፍጻሜ እየኖርን እንዳለ፡ በእውነት እናምናለን። ነቢዩ፦ “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል” ብሎ እንደተናገረ። እኛም ዛሬ፡ በጸጋህ ለዚህ ታላቅ የወንጌል ብርሃን ተላላኪዎች መሆናችንን በማመን፡ ይህ መነቃቃት ወደ ሄደበት እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ፡ እንድንሸከም ፈቅደሃል።

19 እኔም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ወንድሞቼ፡ ለአንተ ያለኝ፡ የሕይወቴ ዓላማ፡ እና አሳብ እንዲረዱት፡ መግለጽ እንድችልና እንድትፈቅድልኝ ከልቤ እጸልያለሁ። በወንጌል ስራ ሁሉ፡ ፍፁም ፍቅር፡ ህብረት፡ እና የጋራ-አብሮነት እንዲኖረን፡ ሰጠን። እሱና አባቱ አንድ እንደነበሩ አንድ እንድንሆን በጸለየው፡ በኢየሱስ ስም፡ እንጠይቃለንና። ይህም፡ “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ሲኖራችሁ፡ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ፡ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ፡” ያልከውን በማመን ነው። አሜን።

20 አሁንም… ወንድሞች እና እህቶች ሆይ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ እንዳልወለድኳችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። ይሁን እንጂ ሌሎች የሚሉት ነገር ከመሰማት እንድትቆጠቡ፡ ራሴን ለእናንተ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ ብዬ አሰቤአለሁ። አገልግሎት በተካሄዱባቸው በሌሎች ጉባኤዎች ላይ፡ ብዙ ጊዜ ገልጬዋለሁ፡ ለቺካጎ ቡድን ግን፡ ይህ የመጀመሪያዬ ነው፣ እኔ ለማድረግ እየሞክርኩት ያለሁትንና፡ ራሴንም በደንብ ማስተዋወቅ እፈልጋለሁ።

21 በተባረከው ጥንታዊ ወንጌል፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 26፡ እንዲህ እናነባለን:

**ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፡ ስለዚህ፡ ከሰማይ ለታየኝ ራእይ እምቢ አላልሁም:**

22 ይህ፡ በእርግጥ፡ ጳውሎስ የተናገረው ነው። እሱንም፡ እንደ አገልጋዮች፡ እኛ እሱን ዋቢ ማድረግ፡ እንወዳለን፡ ምክንያቱ… በአንድ ልብ፡ የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ መሆኑን፡ ሁላችንም እናምናለን፡ እግዚአብሔር—ለአሕዛብ ምስክር ይሆን ዘንድ እሱን ጠራው። አገልግሎቱም ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ነበር።

23 ብዙ ጊዜ፡ ያልተለመደ ነገር በተንሳ ቁጥር፡ ጥያቄ ይቀሰቅሳልና። ይህም፡ ልክ እንደሆነ አስባለሁ፡ ጥያቄ ማስነሣቱ ተገቢ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ፓስተሮች፡ በሚሰሙት ነገር ተጠራጣሪ ናቸው—የመጠራጠር መብት ያላቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም፡ **ፓስተር** የሚለውን ቃል ትርጉም ከተረዳሁት፡ “እረኛ” ማለት ነው። ስለዚህ፡ መ—መ—መጋቢ፡ ወይም፡ እረኛ ማለትም ነው፡ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ህብረት የወንዶችና የሴቶች የበላይ ጠባቂ ያደረገው ሰው ነው። በጎቹ ምን አይነት ምግብ እየተመገቡ እንዳሉና፡ ከየት እንደሚመጣ የማወቅ መብት አለው። ለዚህ መብት ያለው ይመስለኛል።

24 እና አንዳንዴ፡ ሰዎች፡ ወይም ፓስተሩ የተጠራጠሩ ቢመስሉ፡ ያ፡ በጭራሽ፡ ማንንም ማስጨነቅ የለበትም። ለቆመላቸው፡ ጥያቄ ለተፈጠረበት፡ የራሳቸው ሰው፡ የሰው ሁሉ ልብ ሊያከብረው ብቻ ይገባል። በትክክልም’ኮ፡ መስመራችሁን እንደጠበቃችሁ፡ እርግጠኞች ካልሆናችሁ፡ በእምነት እንዴት መጓዝ ትችላላልችሁ?

25 አእምሮአችሁ ከተጠቀማችሁ… በርግጥ፡ ሳይኮሎጂ ይመስላል፡ ምናልባትም ይሆናል፡ ደግሞም ነው፡ ይሁን ችግር የለውም። እንደው፡ ከልባችሁ ግን፡ ከጠረጴዛው አልነሳም ብላችሁ ካሠባችሁ፡ ላትነሡ ትችላላችሁ። አያችሁ? ማመን… ቀላል ነው።

26 ልታምኑ ይገባል። እምነት ሊኖራችሁ ይገባል። ድፍረት ሊኖራችሁ ይገባል። ወዴት እንደምትሄዱ ካላወቃችሁ ግን—ድፍረት እንዴት ሊኖራችሁ ይችላል? ከዚህ በፊት ባልሄድኩበት መንገድና፡ ኩርባ ሁሉ፡ ቀጥሎ ባለው

ኩርባ ምን እንደሚገጥመኝ ሳላውቅ፡ ከመጠን በላይ እያሽከረከርኩ እንዴት እሄዳለሁ? ወዴት እንደምትሄድ ማየት አለብህ፡ ካልሆነ ግን እንዴት መራመድ እንዳለብህ አታውቅም። ሁሉም ሰውም እንደዚህ መሆን አለበት። ከዚያ ስትችል፡ ታያለህ፡ ይገለጽልሃል፡ ወዴት እንደምትሄድም ታውቃለህ፡ ከዛ በኋላ የሚያግድህ የለም።

27 ጳውሎስ፡ ለአግሪጳ ለማለት እየሞከረ የነበረው፡ ይኸው፡ ይመስለኛል። እሱም—እንዲህ፡ አላቸው፡ “ድሮ እንደእናንተ ነበርኩ።”

28 እና ምናልባት፡ ምናልባት፡ ይህ—የባፕቲስት ወንድም፡ ዛሬ ጠዋት ከሚስቱ ጋር ወደ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን፡ መሄድ ቢችል ኖሮ፡ ምስክርነታቸው ይህ ይሆን ነበር። “ድሮ—እንደእናንተ ነበርኩ።”

29 ወይም፡ የቸርች ኦፍ ክራይስት፡ ወይም እዚህ ያለው—ካምቤላይት ወንድማችን፡ ወደ ህዝቡ—ቢሄድ ኖሮ ያው ነው። ይመስለኛል፡ ዲሳይፕልስ ኦፍ ክራይስት፡ ብለው በተሻለ ስያሜ ይጠሩታል፡ ይሁን እንጂ የአሌክሳንደር ካምቤል ዶክትሪን ነው። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ግን በሙዚቃ ምክንያት፡ ከውስጥህ ወጥታለች። ትክክል ነው አይደል? ወደ እነርሱ መመለስ ቢችል፡ “ድሮ እንደ እናንተ ነበርኩ፡” ይላቸው ነበር።

30 ጳውሎስም ወደ ንጉሡ ወደ አግሪጳና ወደ ፊስጦስ ቀረበና፡ “ድሮ እንደ እናንተ ነበርኩ። የፈሪሳውያን ፈሪሳዊ ነበርኩ። በታላቁ መምህር በገማልያል ሥር እንዳደገ፡ ሥርዓታቸውንና ወጋቸውን ሁሉ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ፡ የሚያምኑት እና የማያምኑትን ሁሉ ተናገረ። “የእግዚአብሄር ቤተ ክርስትያንን እስከ ሞት ድረስ አሳዳጅ ነበርኩ፡” አላቸው። አያችሁ? “አሁን እኔ በተራዬ ስለምጠየቅበት ነገር፡ አሳዳጁ ነበርኩ፡” አላቸው።

31 እኔ የእስጢፋኖስ ሞት ተጠያቂው ጳውሎስ መሆን አለበት እያልኩ ሁል ጊዜ አስብ ነበር፡ ምክንያቱ የከበረ የእስጢፋኖስ ፊትን እያየ ነበርና። የሚገድሉት ድንጋዮች እያረፉበት፡ ወደ ሰማይ አይቶ፡ “ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ፡” ሲል ነበርና። ታውቃላችሁ፣ መልእክተኛውን ልትገድሉት ትችላላችሁ፡ መልእክቱን ግን በፍጹም መግደል አትችሉም። ምንም እንኳን እስጢፋኖስ፡ ከጌታ ጋር ለመሆን፡ ቢሄድም፡ ሐዋርያት ተብሎ እንዲጠራ፡ የማይገባው፡ እንዲሁም፡ ከሁሉ ይልቅ “ታናሽ” የሆነው ጳውሎስ፡ ስለሱ መናገሩን ስለቀጠለ፡ መልእክቱ አልቆመም፡ ይህም እሱ ራሱ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ሲወገድ—ፍቃድ ሰጥቶ ተባባሪ ነበርና።

32 ስለዚህም፡ ጳውሎስ፡ ሰዎች በሰው ፊት እንደሚያደርጉት ሁሉ፡ ከመጀመርያ የነበረውን፡ የራሱን—ልምምድ አሁን ወደደረሰበት፡ አመጣውና፤ አሁን የሚሰራው ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ለማሳየት፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት አስያዘው። ከእምነታቸው ጋር የሚቃረን ቢሆንም፡ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን እያሳያቸው ነበር።

33 ስለዚህ፡ ይመስለኛል... እናንተ፡ በስብሰባ ላይ የነበራችሁ፡ ወንድሞች፡ ብዙ ጊዜ እንዳልኩት፡ እኔም ልሁን ሌላ ወንድም፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ነገሮች፡ ሲናገር ካገኛችሁት... ተጠራርተን፡ መነጋገራችን እውነት ይሆናል፡ “ያ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለምና፡” አያችሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ

ከሆነ፡ ምናልባት የተለየ ትርጉም ሊኖራችሁ ይችላል፡ ይሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለ፡ ደህና ነው።

34 አሁን፡ ጳውሎስ ነቢዩ የተናገረውን፡ እና ሙሴ የተናገረው፡ እየተፈጸመ ያለውን ትርጓሜ እየሰጠ ነበር። ኢየሱስንም በመንገድ ላይ በራእይ ተገናኘው። ኢየሱስም እርሱን ጠራው።

35 ለአይሁዶች፡ እርሱ እንዳለው፡ ከባድ ነገር ሊሆንባቸው ባልተገባ ነበር፡ "እጅግ የተከበረ ፊሰጦስ፡" ሌላ—ሌላ ነገሮች፡ ዘረዘረ... "እግዚአብሔር ሙታንን የሚያስነሣ እንደ ሆነ፡ በእናንተ ዘንድ የማይታመን ነገር ነውን?" አያችሁ? "እግዚአብሔር—በቀድሞ ዘመን ያደረገውን ነገር፡ ከቃሉ የምታውቅ ከሆንክ፡ ሙታን ማስነሣት እንደሚችል በርግጥ ታምናለህ።"

36 በመቀጠል፡ ወደ ደማስቆ ሲሄድ በመንገድ የገጠመውን ነገር፡ ያጫውታቸው ጀመረ፡ ይህም፡ ስለሱ በመሰበኩ ብዙዎች የሚንጫጩበት ይህ ኢየሱስ—በዘመናት ሁሉ ሲያገለግሉት የነበረው፡ ራሱ አምላካቸው እንደሆነ እንዲያሳውቃቸው ነው። ምክንያቱ፡ በምድረ በዳ ከእነርሱ ጋር የነበረው፡ ያንን ብርሃን ሆኖ፡ የእሳት ዓምድ ሆኖ የመራቸው፡ እሳት፡ እሱ ነውና። በተመሳሳይ መልኩ፡ አሁንም የሚያሳውር ብርሃን ሆኖ፡ ለጳውሎስ ታየው። እርሱም፡ "ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ፡" ብሎ ጠየቀ?

37 እርሱም "አንተ የምታሳድደኝ፡ እኔ ኢየሱስ ነኝ። የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል፡" ብሎ መለሰለት።

38 ይህም ሁሉ ምን እንደሆነ ሊያስረዳቸው ሞከረ፡ እና—ሕዝብ ፊት ሊያቀርበው የፈልገውን ነገር ምን እንደሆነ ሊያስተምራቸው ፈለገ፡ ይህም፡ ደግሞ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሑ እንደሆነ፡" እና፡ "እንደሞተ፡ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው ነው።" ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ነበር። አሁንም እሱ፡ "አሁን ወደ እግዚአብሔር አብ፡ ወደ ላይ እንደ አረገ፡" እርሱም ስለ—ትንሣኤው ምስክር እንደሆነ መሰከረ። አሁንም፡ እነኚህ፡ በህዝብ ሁሉ ፊት እንግዳ የነበሩ፡ ድንቆች፡ ተአምራቶች፡ እና ምልክቶች፡ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ የተናገራቸው ነገሮች ስለሆኑ፡ ለእውነተኛ እና በቅዱስ ቃል ለሚያምን ሰው አዳዲስ ነገሮች አይደሉም።

39 የመሲሑ መምጣትና፡ ሲመጣ ምን እንደሚያደርግ፡ ትንቢቱ እንዴት እንደተሰጠ፡ ምን እንደተባለ፡ ወደ ነቢያት መለስ ብለን እንመልከት፡ ከኢሳይያስ 35 "አንካሳው እንደ እምቦሳ ይዘላል፡" እና የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ሊጠቅስ ይችል ነበር። እዚህ የተጻፈ የለም፡ ነገር ግን ምናልባት ወደ ኋላ ሄዶ በነገስታቱ ፊት ባቀረበው አጭር ንግግር ውስጥ ይጠቅሰዋል፡ ምክንያቱ፡ እናንተ እኔን እንደምትታገሱኝ ሆነው እሱን አይታገሱትም። ስለዚህ፡ እሱ—ሲያብራራላቸው፡ እናገለግለዋለን የሚሉት አምላክ ራሱ...

40 እንደገናም፡ እንዲህ አላቸው፡- "**መናፍቅ** ተብሎ በሚጠራው መንገድ፡" አቤት፡ "ይገርማል'ኮ" አያችሁ። "እናንተ መናፍቅ ብላችሁ በምትጠሩት መንገድ፡ አመልከዋለሁ።" አያችሁ፡ "መናፍቅ ተብሎ በሚጠራው መንገድ።"

41 እርግጠኛ ነኝ፡ ዛሬ እንደ ፕሪስባይቴሪያን፡ እንደ ካቶሊክ፡ እንደነ ባፕቲስት ካሉ፡ ሌሎችም፡ ያንን ወንድም በስነ አእምሮ ክፍል፡ ወይም፡ መሰል ነገር ውስጥ ለማስገባት በፈለጉ፡ የቀድሞ አብያተ ክርስቲያናት ፊት፡ ብንቆም፡

ተመሳሳይ ምስክርነት ልንሰጥ እንችላለን። “መናፍቅ ተብሎ በሚጠራው መንገድ፡ የአባቶቻችንን አምላክ የማመልከው በዚህ መንገድ ነው።”

42 በአግሪጳም ፊት ያደረገው ንግግር እንዴት ያለ ታላቅ ምስክር ነበረ፡ በንግግሩ መካከል፡ አግሪጳ ጮኸ፡ “ጳውሎስ፡ ሳውል ሆይ፡ ክርስቲያን እንድሆን ልታሳምነኝ ቀረብክ’ኮ፡” እስኪል ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስን፡ እንዴት አድርጎ በግልጽ እንደ ተናገረ አያችሁ፡ ይሁን እንጂ ከሱ ሙኩሩብ ጋር የሚቃረን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ “እንዳንተ እንድሆን ልታሳምነኝ ተቃረብ’ኮ፡” እስኪለው ድረስ፡ እጅግ ግልጽ ነበር።

43 ጳውሎስም እንዲህ አለ፦ “ከዚህ እስራቴ በቀር፡ ሁላችሁ፡ እንደ እኔ በሆናችሁ ብዬ እመኛለሁ አላቸው፡” አያችሁ፡ እንደሱ ዓይነት አማኞች እንዲሆኑ ነው። ማለት፡ በሌላ አነጋገር… “እኔ እንደማየው—እናንተም መገለጡን እንድታዩ በእግዚአብሄር ፊት እመኛለሁ።” በሌላ አነጋገር፡ “ያንን ማድረግ ቢቻላችሁ—ምኞቴ ነበር።” አያችሁ? “እንድትሆኑም እመኛለሁ።”

44 ፊስጦስ፡ ይመስለኛል፡ “ከትምህርት ብዛት፡” ራስን ስተሃል “አብድሃል፡” ብሎታል። እሱ ግን የያዘውን አስረግጦ እንደሚያውቅ እንጂ—እንዳላበደ፡ እንዲያውቅ—አደረገው።

45 እና ወንድሞች ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይህን እላለሁ። ምናልባት በዚህ ሁሉ… የጳውሎስን ሕይወት ለማሳየት ሳይሆን፡ ትንሽ መሠረታዊ ንግግር ለመስጠት ነው። ምናልባትም፡ ዛሬ ጠዋት የሚናገሩ ሌሎች ይኖራሉና፡ እኔ ግን ይህን ለመናገር እድሉን እጠቀምበታለሁ። እኔም እንደው ሲጠሩ የሰሟኋቸው፡ አብያተ ክርስትያናት በሙሉ፡ እነ ቤተል ቴምፕል፣ ኢንዲፐንደንት፣ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፣ እና ሌሎች በሙሉ… ሁላችሁም በአንድነት እኔ ማየት የምችለው፡ እናንተም እንድትችሉ፡ ማየት በቻላችሁ ብዬ እመኛለሁ። የማየውን ራዕይ ብታዩ ኖሮ፡ አገልግሎቱን፡ የበለጠ ግልጽ ሆኖ ትረዱት ነበር።

46 ባፕቲስት ቤተ ክርስትያንን ትቼ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ስመጣ፡ በሚሲዮናዊ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የሾመኝ ዶክተር ሮይ ኢ ዴቪስ፡ የጌታ ራእይ አይቼ፡ በነገርኩት ጊዜ—አቃዥቶሃል ብሎ ተናግሮኝ ነበር። በዚያን ጊዜ—ስለ ፈውስ ምን ይባል እንደነበረ ታውቃላችሁ፡ ተራ ደረጃ ላይ ነበር።

47 እኔም—ስለጴንጤቆሴዎች ምንም አላውቅም ነበር። ወለሉ ላይ ተዘርግተው እንደ እብድ ውሾች የሚሽከረከሩ ሆሊ-ሮለሮች ስብስብ መሆናቸውን፡ በማራገቢያ አቀዝቅዘው እንደገና ወደ ልባቸው እንደሚመልሷቸው፡ ወዘተረፈ እሰማ ነበር። ስለ ጴንጤቆስጤ ሰዎች የማውቀው ያ ብቻ ነበር።

“እነማን ይሰሙኛል ብለህ አሰበህ ነው? ” አለኝ፡

48 “የላከኝ እግዚአብሔር ከሆነ፡ የሚልከኝ ስፍራ እና ህዝብ አለው፡” አልኩት። ትክክል ነው። አያችሁ? “ምክንያቱ፡” አልኩት፡ “ዶክተር ዴቪስ፡” አልኩት፡ “ቆሜ እንደማይ ሆኖ፡ በግልጽ አይቼዋለሁ፡” አልኩት። ስለ ራእዮቹም እንዲህ አሉኝ…

49 ወንድሞቼ ሆይ፡ እኔ ብርቱ አማኝ ነኝ፡ ስጦታዎች እና ጥሪዎች—ንስሓ አይጠይቁም። እኔ ይሄን—አምናለሁ። ከተወለድኩ በኋላ፡ ያልሆንኩው

ነገር መሆን አትችልም። ያልሆንከው ነገር ለመሆን የምትሞክር ከሆንክ፡ የግብዝ ጨዋታ እየተጫወትክ ነህ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ግብዝ ከመሆኔ በፊት ልሙት። ራሴን አድርገኝ፡ የበለጠ ብሩህ እና ግልጽ ሰው አድርገኝ። እና—እና፡ እንግዲህ፡ አቤቱ እንዲያ ልሁን፡ ሰው ሁሉ በዚያ ይወቀኝ። ከዚያ እውነትን ታውቁታላችሁና።

50 አሁንም፡ እንደምታውቁት፡ እንዳልኩትም፡ ብዙ የተማረ ሰው አይደለሁም። ስለዚህ... በቲኦሎጂ፡ ከሁሉም ይልቅ ታናሽ እኔ ነኝ። ታውቃላችሁ ብዬ አስባለሁ፡ አያችሁ። እንደ ሰባኪም፡ ሰባኪ ነኝ ማለት አልችልም፡ ትምህርት ባለማግኘቴ እና ቃላትን ባለማወቄ፡ እና ወዘተረፈ። ይሁን እንጂ፡ በጸጋው፡ ባለችኝ ትንሿ እውቀት... ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ባወቅኳት፡ እውቀቴ፡ ወንድሞቼ ሁሉ በየሰፍራው የሚያካፍሉትን ነገር፡ እኔም አብሬ ለማካፈል እሞክራለሁ።

51 መጀመርያ የገባሁባት፡ የተሾምኩባት፡ ብቸኛዋ ቤተ ክርስትያን... ባፕቲስት ቤተ ክርስትያን፡ ከተውኩ በኋላ። የተሾምኩት በ1933፡ በሚሰዮን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ውስጥ ነው። የ—የ... የደቡብ ባፕቲስት ኮንቬንሽን አባል ነበረች። እና፡ በጊዜው፡ ትቼ... በወጣሁ ሰዓት...

52 እንግዲህ፡ የባፕቲስት ቤተ ክርስትያን ሉአላዊ ቤተ ክርትያን ነው። ሁላችንም—እናውቃለን፡ እንዲሁ—ነውና... ጉባኤው እስከተቀበላችሁ ድረስ፡ የወደዳችሁትን ነገር መሰበክ ትችላላችሁ። እነሱ... መሰበክ የፈለግከውን ሰበክ ነው።

53 እኔም ይህን እወደዋለሁ፡ አያችሁ፡ ሐዋርያዊ ነውና። ምክንያቱ፡ በቤተ ክርስትያን ውስጥ፡ የበላይ የሚሆን፡ እረኛ የሚሆን፡ ፓስተር እንደሆነ እንገነዘባለንና። እና—እና—አንድ ቢሾፖ... ወይም ሌላ ሰው ከፓስተሩ አልፈው መገለጡን የሚያፈርጡት ከሆነ፡ ታዲያ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንዴት ይሠራል? አያችሁ፡ ልታገኙት አትችሉም። ስለዚህ፡ እኔም...

54 ከዚያ ሰወጣ፡ ከመጀመሪያው ጎራ ጋር ተዋወቅኩኝ፡ ይህም በሴንት ሉዊስ፡ ሚዙሪ የትንሿ ቤቲ ዳገርቲ፡ ፈውስ በሆነ ጊዜ ነው። የተባበሩት ጴንጤቆስጤ፡ ወይም የኢየሱስ ስም ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ነበር፡ በዚያም ፓስተሩ፡ ታናሽ ልጁ ተፈወሰች። እውነቱን ለመናገር፡ ጴንጤቆስጤ እንዲባሉ ያስቻላቸው "ኦንሊ ጂሰስ፡" ተብለው በመጠራታቸው፡ ብቻ ይመስለኝ ነበር። ጴንጤቆስጤ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ያ ነው ብዬ አሰብ ነበር፡ ምክንያቱ እራሳቸውን እንደዛ ብለው ይጠሩ ነበርና፡ ልዩነቱም ይህ ይመስለኝ ነበር። ስለዚህ፡ እንግዲህ፡ ከዛ በመነሣት ቀጠልኩ...

55 ጥሩ ሰው ነው፡ በሴንት ሉዊስ ታላቅ ሰብሰባ አደረግን፡ ያም ሰዕል የታየበት ነው። እና በኪዬል አዳራሽ ነበርን፡ በመጀመሪያውም ወይም በሁለተኛው ምሽት፡ አሥራ አራት ሺህ ህዝብ ተሰብሰቦ ነበር፡ ፖሊሶችን በሮች ላይ መድበን... እና እነሱን መቆጣጠር፡ አልቻልንም።

56 ከዚያ ተነሥተን፡ በጆንሰቦሮ ወደሚገኘው የብለሰድ ኦል ባይብል ሃወር ተበርናክል፡ ወደ ሆነው ወደ ሪቻርድ ቲ ሪድ ወረድን፡ እሱም ተመሳሳይ ድርጅት

ነበር። ከዚያ ወደ ዶክተር ጂ ኤች ብራውን፡ ተመሳሳይ ድርጅት፡ በ 505 ቪክቶር ጎዳና በሊትል ሮክ፡ አርካንሳስ። ከዚያ፡ ወደ ዌስት ኮስት ወረድን።

57 ወደ ዌስት ኮስት በገባን ጊዜ፡ እሳቱን ቆሰቆስኩት። ከዚያም በጴንጤቆስጤ ሰዎች መካከል፡ በየድርጅታቸው ልዩ ልዩ ዓይነት እንዳለ ተረዳሁ፡ ልክ እንደ እኛ እንደ ባፕቲስቶች። እያችሁ፡ የተለያዩና—እጅግ ብዙ ዓይነት ነበሩ፡ ከዚያም፡ ልዩነት ነበሯቸው። አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፣ እና ቸርች ኦፍ ጋድ፣ እና ሌላ ዓይነት፣ ሌላ ዓይነት፣ ሌላ ዓይነት፣ እና—ልዩ ልዩ ናቸው። እነሱም ተለያይተው፡ በመካከላቸው ትንንሽ ድንበሮች አሰምረዋል። እና ሌሎቹ ወንድሞችም ወደ እኔ እየመጡ፡ “አንተ፡ ከነ እከሌ ጋር፡ ኦንሊ ጂሰስ ነህ፡” ይሉኝ ጀመር።

እኔም “አይደለሁም፡ እንዲህ ነኝ—ብዬ ራሴን አልጠራም፡” እላቸው ነበር። እያችሁ?

“ከእነርሱ ጋር ህብረት ታደርግ፡ የለም’ዴ፡” አለኝ።

58 እኔም “ታዲያ፡ ይሄ’ኮ—እንደነሱ አያደርገኝም፡” አልኩት። እያችሁ? “በ—በ—በቃ… ወንድሞቼ ናቸው፡” አልኩት።

59 አለኝም፡ “እነሱ’ኮ፡ ዝም ብለው ናቸው… እንዴ፡ ሁሉም፡ ተራ፡ የቡዛርድ ሩትስ ምናምንቴዎች ናቸው። ምንም… ”

60 እኔም አልኩት፦ “አሁን፡ ይቅርታ አርግልኝ። በመካከላቸው ጥሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ተዋውቄአለሁ። የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው።” “ክፉዎች ሳይሆኑ፡ ክፉዎች፡ ብለህ ስለጠራሃቸው—በጣም አዝኜብሃለሁ፡” አልኩት።

61 ከዛ በኋላ፡ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይወስድብኝ፡ ቶሎ ብዬ አቋረጥኩት። ከዛ በኋላ፡ ሐሳባቸው ምን እንደሆነ፡ ልዩነታቸው ምን እንደሆነ፡ እንዲለያዩ ያደረጋቸውን ነገር ማጥናት ጀመርኩ። እና ከሁለቱ ታላላቅ ቡድኖች መካከል አንዱ፡ ኦንሊ ጂሰስ፡ እንደሚባል ደረሰኩበት፡ ሌላኛው ደግሞ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ይባላል። እና በውኃ ጥምቀት ላይ፡ አለመግባባት ነበረባቸው፡ ወይም ተለያይተዋል፤ አንደኛው ጎራ “አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፣” ይጠቀማል፡ ሌላኛው ደግሞ “በኢየሱስ” ስም ይላል።

62 እሺ፡ ሳያቸው፡ በሁለቱም በኩል ታላላቅ ሰዎች፡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩና። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “አምላክ ሆይ፡ ወደ ፊት ሁሉም አንድ ሆነው… በአንድነት ባያቸው… ብቻ ‘እርስ በርሳችን አንገናኝም’ እንዳይሉ፡ መስመራቸውን ብቻ አታሰምርባቸው።” በዚህ ጊዜ፡ እርኩስ መንፈስ በመካከላቸው ገብቶ፡ በመካከላቸው በተነሱ ጉዳዮች ላይ ጥላቻን፡ እና ክፋትን እንዳሰከተለ አይቻለሁ። ሳሰበው፡ “ዲያቢሎስ የሚፈልገው በትክክል ይህ ነው። ፍላጎቱ ይህ ብቻ ነው።” ጠመንጃዎቻችሁ እንዳችሁ በእንዳችሁ ላይ እንዲሆን ከአስተማሪ፡ ከተሽናፊዎች ጋር መዋጋት አያስፈልገውም። እናም…

63 ኋላ ላይ፡ መጨረሻ ላይ፡ ወደ ትርኢቱ ደረሰ። እና ትርኢቱ በ1946 በሲያትል፣ ዋሽንግተን ነበር። እና አንድ ቀን ጠዋት፡ ጥቂት አገልጋዮች ባሉበት—ወደተዘጋጀ ቁርስ፡ እንደዚህ አይነት የሆቴል ሎቢ ወሰዱኝ። እና ሁለት ዋና ሰዎችን ማነጋገር ነበረብኝ።

64 አንደኛው ዶክተር ኔስ ነው። ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ የሆናችሁ ወንድሞች እንደምታውቁት አስባለሁ። በሰሜን ምዕራብ ግዛት ውስጥ ይኖር ነበር፤ ታላቅ ሰው፣ ብልህ፣ ምሁር። እና የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ወክሎ ነበር።

65 ሌላኛው፡ ከዩናይትድ ጴንጤቆስጣል ቤተ ክርስቲያን ዶክተር ሲዝም ነው። የዩናይትድ ጴንጤቆስጣል ቤተ ክርስቲያን ወንድሞች ታስታውሱታላችሁ ብዬ እገምታለሁ። እሱም በሰሜን ምዕራብ ግዛቶች ይኖር ነበር፡በእነዚያ ወረዳዎች እና በአውራጃዎቹ ላይ ኃላፊ ነበረ።

66 እንግዲህ ሁለቱ ሰዎች ተገናኙ። እኔም እነርሱ ጋር መገኘት ነበረብኝ፡ ምክንያቱም ሰይፋቸውን እየሳሉ ስለነበሩ፡ በሁሉም ወገን ይቆርጠኝ ነበርና። እና “ምን ማድረግ አለብኝ? ምን ላድርግ? ብዬ አሰብኩ፤

67 እንግዲህ፡ አሁን፡ አሉኝ፡- “በዚህ ነገር፡ ከአንዳችን ጋር መወገን አለብህ። ከኦንሊ ጂሰስ የምትሄድ ከሆነ፡ ኦንሊ ጂሰስ መሆን አለብህ። ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ከሄድክ ደግሞ፡ ኦንሊ ጂሰስን ለቀቅ አድርግና፡ ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ጋር ሁን፡ ወዘተረፈ።” የሆነ ነገር ማሳየት ወዳለብኝ ሁኔታ አደረሱኝ።

68 በዚያን ቀን ጠዋት ከመውረዴ በፊት ብዙ ጸለይሁ። እኔም፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ሁለት ታላላቅ ሰዎችና። በሺዎች የሚቆጠሩ፡ አገልጋዮች አሉና፡ እርዳኝ አልኩት። አገልግሎት ሰጠህ ወደዚህ ልከኸኛልና። ሁለቱም ባርያዎችህ ናቸውና። እና አንዱን ድርጅት ሌላውን እየታገለ ባለበት በዚህ ጊዜ ይህች ያለችኝ ትንሿ ተጽዕኖ ለአንዱ ድርጅት ብቻ ልጣልለትን? ” አያችሁ? “ይህን በማድረጌ—ልክ እንደሆንኩ አይሰማኝም። ይህን ማድረጌ የክርስቶስ ፈቃድ የሚሆን አይመስለኝም።” እና “እግዚአብሔር ሆይ፡ እርዳኝ የምሰራውን ነገር ስጠኝ፡ ወይም የምናገረውን ስጠኝ” አልኩት።

69 በዚያ ማለዳ፡ ከጎኔ ማንም አልነበረም። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለብቻዬ ቆምኩኝ እንጂ።

70 “ወደፊት የምታረገው ነገር ምንድነው? ምን—ምን—ምን ትወስናለህ? ” እንግዲህ ታላቁ ክርክር፡ ተጀመረ።

71 እኔም አልኋቸው፡ “እኔ ውሳኔዬን ወሰኛለሁ። ውሳኔዬም፡ ከሁለታችሁ ጋር እቆማለሁ፡ የሁለታችሁ ድርጅት ውስጥ ግን አልገባም፡ ብዬ ወሰኛለሁ፡ ከሁለታችሁ ጋር፡ ተደጋግፌ፡ ‘ወንድማማቾች ነን፡’” እላለሁ አልኳቸው። አያችሁ? አያችሁ፡ ወንድማማች ነን። አያችሁ? አልኋቸው፡- “ይህ እንዴት እንደመጣ ለመረዳት፡ የተለያዩ መጻሕፍቶችን ለማንበብ ሞክሬአለሁ፡ ‘ኢዲሱ ጉዳይ፡’ የሚሉት ምን እንደ ነበር እንዴት እንደተለያዩ፡ **ይሄኛው** እንዴት **በዚህ** እና **በዚያ** መንገድ እንደ ጀመረ።” እንዲህ አልኳቸው፡- “በእናንተ እንዳለው ክርክር፣” “ያኔም ከጴንጤቆስጤ በኋላ ያንን እንቅስቃሴ፡ ጴንጤቆስጤን… የሰበረው ይህ ነበር። እርስ በርሳቸው ጭቅጭቅ ስለጀመሩ ነው።” “እና ነገሩ እንደገና ተሰበረ፡” አልኳቸው።

72 “ወንድሞች ሆይ በእናንተ መካከል መካከለኛ ሊሆን የሚቻልበት ዕድል አለ ወይ? አልኳቸው፡ ሊቆምላችሁ የሚችል—አለ ወይ? ”

73 ፊት ለፊት ስለነበረ፡ እንዳቸውም፡ አፋቸውን አልከፈቱም። ከአስራ አምስት፡ ከሃያ ዓመታት በፊት፡ እንዴት እንደነበረ፡ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም አንዱ ቡድን ከሌላው ተነጥሎ ወጥቶ ስለነበር፡ ብዙ ጠብ ነበረ።

74 አልኳቸው፦ "እንግዲህ፡ ወንድሞች ሆይ፡ እኔ የማደርገው ይህ ነው። እኔ የማደርገው... በመስረቱ እግዚአብሔር አጥምቅ ብሎ አልላከኝም። ለታመሙ ልጆቹ እንድጸልይ ነው የላከኝ።" እንዲህ አልኳልቸ፦ "ስለዚህ፡ እኔ—ለታመሙ ልጆች ለመጸለይ ልሂድ፡ እናንተም አገልጋዮች ጥምቀታችሁን አድርጉ፡" አልኳቸው።

75 እንዲህ አልኳቸው፦ "አሁን እናንተም እንድትረዱት፡ አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ።" እንዲህ አልኩት፦ "ወንድም ኔስ፡ እነዚህ... በኢየሱስ ስም የሚሉ ሰዎች፡ እናንተ በአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ውስጥ እንደምታደርጉት በተመሳሰይ መልኩ በልሳን ሲናገሩ መንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ታምናለህን? "

"አዎን፡" አለኝ።

76 አንተስ፡ "ወንድም ሲዝም፡ እናንተ በጥምቀት ጊዜ እንደምታደርጉት እነዚህ አሴምቢሊስ ኦፍ ጋድ በልሳን ሲናገሩ እናንተም የምታደርጉት ሲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ታምናለህን? "

"አዎን፡ አምናለሁ፡" አለኝ።

77 "እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ 'እግዚአብሄር ለሚታዘዙት መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል ይላልና፡' አሁን፡ ከሁለታችሁ የታዘዘው ማን ነው? አልኳቸው። የታዘዘው ማን ነው? ማንኛችሁ ታዘዛችሁት? እግዚአብሔር ለሁለታችሁ መንፈስ ቅዱስ ሰጥቷችኋል።" አያችሁ?

78 "ወንድም ሲዝም ሆይ፡ ወንድም ኔስ መንፈስ ቅዱስ የለውም፡ ትላለህን? " አልኩት፡

"አልልም፡" አለኝ።

79 "ወንድም ሲዝም መንፈስ ቅዱስ አልተሞላም ትላለህን? " አልኩት

80 "አልልም።" አያችሁ? ሁለቱም፡ አንዱ ሌላውን መንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ አመኑ።

81 አያችሁ ግን፡ ወንድሞች ሆይ፡ ትርጉም እንኳን አይሰጥም'ኮ። ትርጉም አይሰጥም። ከዚያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፡ ሰማሁ...

ከእፍታ በኋላ ወደ ነጥቤ እመለሰበታለሁ።

82 ከፊንላንድን ከተመለስኩ በኋላ፡ እዚህ ያሉት የፊንላንድ ወንድሞች፡ ያ ጉባኤ፡ እግዚአብሔር ከሰጠን፡ ከታላላቅ ጉባኤዎቻችን አንዱ እንደሆነ አስባለሁ። የሞተ የህጻን ልጅ አካል የተነሳበት፡ ሌላ ብዙ ነገር፡ የተከናወነበት ጉባኤ ነው። በሰቶክሆልም፡ ሰዊድን፡ እዚያ ከሚገኘው የፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ከሊዊ ፔትረስ ጋር ተገናኘን ይህም የፊላደልፊያ ቤተ ክርትያን ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ወንድም ጎርደን ሊንሴይ፡ እንደሚመስለኝ... አሁን፡ አባላቸው አይመስለኝም፡ ድሮ ግን አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ነበረ።

83 እና አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፡ በኢንተርናሽናል ደረጃ፡ ዋና ስፖንሰሮቹ ናቸው። ፎርሰኬር የሚባለው፡ አሁን ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ራሱን-አግልሎ

የወጣውም፡ ታላቅ ሰፖንሰሬ ነበሩ። በአለም አቀፍ ደረጃ፡ ከዋኖቹ ሰፖንሰሮቼ አንዱ፡ ዋንነሶች ናቸው። አያችሁ? እና የሾለውን ጠርዞቻቸውን ትቼ፡ ያንን አቋሞ ያዝኩኝ፡ በሁለቱ ንትርክ መካከል ላለመግባት፡ አቋሜን አሰቀመጥኩ። ወንድማማቾች መሆናችን ተመልክተን፡ ወደ አንድነት እስክንመጣ፡ ሁላችንም እየሄድንበት የምንገኘውን፡ የአሳባችን እና የግባችን፡ ትክክለኛ ነጥብ—ማየት እስክንችል ድረስ ነው።

84 እናንተም፡ አስቀድማችሁ—አሳባችሁ እና ግባችሁ መመርመር አለባችሁ። በመጀመሪያ፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተረዱ፡ ከዚያ ግባችሁን ተረዱ፡ ከዛ አሳባችሁን ፈትሻችሁ ትክክለኛ አሳብ እንዳላችሁ እወቁ። ከዚያም፡ ኢየሱስ በማርቆስ 11:24፡ እንደተናገረው፡ “በልባችሁ ሳትጠራጥሩ፡ ይህን ተራራ ‘ተንቀሳቀስ፡’ ብትሉት።” ነገር ግን ምንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን፡ በልባችሁ ከተጠራጠራችሁ፡ ወይም የልብ አሳባችሁ ወይም ግባችሁ የተሳሳተ ከሆነ፡ እንዴት ይንቀሳቀሳል? የልባችሁ አሳብ እና ግባችሁ ትክክል እንደሆነ፡ እና የእግዚአብሄር ፈቃድ መሆኑ ሰታውቁ ግን፡ መንቀሳቀሱ የግድ ነው። አለቀ፡ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር የተሳሳተ ነገር ተናግሯል ማለት ነው።

85 በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፡ ወደ መድረክ ሰወጣ፡ እነዚያን ጉዳዮች፡ በመድረክ ላይ ሳነሣ ማንም ሰምቶኝ የማያውቀው፡ ለዚህ ነው። ተወት አደርጋቸዋለሁ። አያችሁ፡ ያ ለእናንተ፡ ትቻለሁ። አያችሁ? እኔ የመጣሁት፡ በመለኮታዊ ጸጋ ለክርስቶስ የሚሆኑ ነፍሳት ማግኘት እንድትችሉ ለማገዝ ነው፡ አያችሁ። አያችሁ? ምንም ልዩነት አይፈጥርም... እናንተ ጥምቀታችሁን አድርጉ። ወደዚህ ሰንመለስ ግን...

86 እርግጥ ነው፡ ሁሉም ነገር ተብያለሁ። ብዙ ተብያለሁ፡ ሰንት ነገር እንደተባልኩ አላውቀውም፡ “ሰጋ የለበሰ የእግዚአብሄር ልጅ” ከመባል—ጀምሮ “ዲያብሎስ” እሰከ—መባል ደርሻለሁ። አዎን፡ ሁሉም ተብያለሁ። ይሁን እንጂ፡ ከዚህ ሁሉ ነገር ጀርባ ግን፡ ወንድማችሁ ነኝ፡ አብሬ የእግዚአብሄር መንግሰት ዜጋ ነኝ፡ ለመንግሰቱ፡ ከእናንተ ጋር አብሬ የሚሰራ ነኝ። ያም እውነት ነው።

87 እንግዲህ አሁን፡ ከተመቻችሁ፡ በቂ ጊዜ እንዳለን ካሰባችሁ፡ እንዴት እንዴት እንደተነጋገርንበት እነግራችኋለሁ። ለጥቂት ደቂቃ፡ ይመቻችኋል፡ ወንድሞች ሆይ፡ ከወንድም ኔሰ እና ከሌሎቹ ጋር? በጣም ጥሩ። በጥቂቱም ቢሆን የሚጠቅማችሁ ይሆናል። የሆነ ነገር፡ እንድታውቁ ይጠቅማችኋል።

88 ከዛ የወሰድኳቸው፡ ጥቂት ነገሮች፡ እዚህ ጽፌ ይዣለሁ። እና ሰለ “ሰላሴ፡” ምን ትላለህ፡ ለመሆኑስ በእግዚአብሔር “ሰላሴ” አለ ወይ ብለው ጠየቁኝ?

89 እንግዲህ፡ እናንተም ወንድሞቼ፡ ይህን ጉዳይ ካጠናቀቅን በኋላ፡ ከተነጋገርንበት በኋላ፡ እንደ ድሮ፡ እንደ ድሮአችን ወንድማማቾች ሆነን እንደምንቀጥል ተሰፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? ነገር ግን ሰዎቻችሁ ወደ ሰብሰባዎቼ ሰለሚመጡ፡ ዕዳ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡ ማናቸውም ቢሆኑ ተታልለው እንዲመለሱ፡ አልፈልግም።

90 መድረክ ላይ ከምሰብከው ነገር፡ ጥያቄዎች ለሚጽፉልኝ ሰዎች ሁልጊዜ እናገራለሁ... ጸሐፊዬ፡ እና ሌሎች ሁሉ በዚህ አሉ። “**ይህ** ምንድነው፡ **ያኛው** ምን ማለት ነው” ብለው ጥያቄ ሲጠይቁኝ?

91 መልሴ፦ “ፓስተራችሁን ጠይቁ ነው፡ አያችሁ። ምክንያቱ፡ መንፈስ ቅዱስን እስክትቀበሉ ድረስ፡ እስከዚህ ድረስ ከመራችሁ፡ ያሻግራችኋል፡ አያችሁ። ይኸውላችሁ፡ ሂዱና፡ ፓስተራችሁን ጠይቁ።” ምክንያቱ፡ እንደዚህ ያሉ ትናንሽ ነገሮች ግራ መጋባትን ያመጣሉ፡ ስለዚህ እርቃለሁ፡ አያችሁ።

92 ሌላው፡ እሱ የድርጅት ተቃዋሚ ነው—ተብያለሁ። አሁንም፡ ይህ አይደለሁም። እኔ እንደማስበው ድርጅቶች በጣም ጥሩ ናቸው፡ ነገር ግን የድርጅታችሁ ስርዓት ሲበላሽ፡ እኔ የምቃወመው ያንኑ ነው። አያችሁ? ዋንነሰም ይሁን፡ ወይም—ሰላሴ፡ ምንም ይሁን፡ ዋናው ስርዓቱ ነው፡ እኛ’ኮ... ማለት ስትጀምሩ፡ ወደዛ ደረጃ አድጋችሁ፡ “እኛ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ነን።”

“ከመንገድ ማዶ ያሉት፡ እነማን ናቸው? ”

93 “ኦህ፡ ወንድሞቻችን ናቸው። ዩናይትድ ጴንጤቆስጣል—ይባላሉ።”

“ማዶ ያሉትስ፡ እነማን ናቸው? ”

94 “ኦህ፡ እነሱ ፎርስኤር ወንድሞቻችን ናቸው። ኦህ፡ ወንድሞች ነን። አንዳችን ከሌላው ጋር፡ ታላቅ አንድነት አለን።”

“ኦህ፡ ሁላችሁም እምነታችሁ አንድ ነው? ”

“ኦህ፡ አዎን፡ እናምናለን።”

“እሺ፡ ታዲያ፡ በዚህ መንገድ እንድትሰሩ ያደረጋችሁ ምንድነው? ”

95 “እንግዲህ፡ **እነዚህ** ወንድሞች **በዚህ** መንገድ ያጠምቃሉ። **እነዚህም** ከእኛ ፊት ለፊት ሆነው **በዚህ** መንገድ ያጠምቃሉ። **እነዚህም** እንዲህ ያጠምቃሉ... ”

96 ወንድሜ፡ በዚያ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ፡ ይህ ነገር ተነጋግረንበታል። አንደኛው ጎራ ሦስት ጊዜ፡ በሆድ በኩል ያጠምቃሉ። ሌላኛውም ሦስት ጊዜ፡ በጀርባ በኩል ያጠምቃሉ። ብለው ጠየቁኝ። እነርሱንም... ጠየቅኳቸው “ይሄን ከየት አገኛችሁት፡” አልኳቸው?

97 አንዱ እንዲህ አለ፡ “በሞተ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ፊት አጎነበሰ ይላልና፡” “እኛም ወደፊት ልናስገባቸው ይገባል፡” አለኝ።

98 ሌላኛውን ቡድን፡ ጠየቅኳቸው፡ “እሺ፡” “እናንተስ... ምን ትላላችሁ? ”

“በሆዱ የሚቀበር ሰው አይተህ ታውቃለህ’ዴ? ” አሉኝ፡

99 እና፡ ምን እንዳደረጉ ታውቃላችሁ? ሁለቱም ተለያዩና ሁለት ጎራ ፈጠሩ፡ ሁለት ድርጅቶች። ኦህ፡ ይቅር ይበለን፡ ወንድሞቼ! ዲያቢሎስ የሚፈልገው ያ ብቻ ነው። የሚፈልገው ይህ ነው። አዎን። በራስህ...

100 አሁን፡ ተመልከቱ፡ ጉዳዩ የአፖስተሊክ ፌይዝ ሚሽን አይደለም፣ ወይም—ማዶ ያሉት፡ የጴንጤቆስጣል አሴምብሊስ አይደለም። ያ አይደለም። እዚህ ጥሩ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፡ በሁለቱም ጎራዎች ጥሩ ሰዎች አሉ። ጉዳዩ ግን፡ አያችሁ፡ የነገሩ ስርዓት ነው።

101 ብዙ ጊዜ እንዳልኩት፡ ልክ እንደ ካቶሊክ ነው። አንድ ሰው ካቶሊክ ሆኖ፡ ስለ መዳኑ ግን በክርስቶስ የተመረኮዘ ከሆነ፡ ይድናል። እውነት፡ እላችኋለሁ። ቤተ ክርስትያን ላይ ከተመረኮዘ ግን፡ ጠፍቷል። እናንተም የጴንጤቆስጤ ወንድሞች ሆይ፡ እኛን ለማዳን ወደ ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ብንመለከት፡ “ከሰዎች መካከል፡ በጣም ጎሰቋላዎች፡ እኛ ነን፡” ትክክል፡ ምክንያቱ ጠፍተናል። ትክክል።

102 “እምነትህ ይላልና፡” ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የምንመለከት ከሆነ ግን ድነናል፡ (ያ፡ ምንድነው? ) ያለቀለት ሥራ ነው። እነዚህ የምንሰራቸው ጥቃቅን ነገሮች፣ የምርት መለዮዎች፡ ብዙ ለውጥ አያመጡም።

103 እና፡ ለወንድም ስኪዝም… እና ወንድም ኔስ፡ “ጥያቄአችሁን ለመመለስ፡” አልኳቸው፣ “ወንድሞቼ፡ የሁለታችሁ ጎራ አልሆንም። ጉራ እስካበዛችሁ ድረስ፡ ሁለታችሁ መሳሳታችሁን፡ አውቃለሁ። አያችሁ? ምክንያቱ፡ ትክክለኛ ዶክትሪን ኖሮኝ፡ ክፉ ልብ ከሚኖረኝ፡ የተሳሳተ ዶክትሪን ኖሮኝ፡ ቅን ልብ ቢኖረኝ እመርጣለሁ።” አያችሁ? “ከሁሉም በላይ፡ አስፈላጊው ነገር የልብ ሁኔታ ነው፡ አልኳቸው።”

104 ይህንም ለማወቅ ቆርጬ፡ ልማድ አድርጌዋለሁ፡ አንድ ሰው፡ ምንም ቢሠራ፡ ምን ያህል የተለየ ቢሆን፡ ወይም ስለ’ኔ ምንም ነገር ቢል፤ እንደ ግዴታ ሳይሆን፡ በልቤ ውስጥ፡ ሌሎቹን እንደምወዳቸው አድርጌ ከልቤ ካልወደድሁት፡ አንድ የተሳሳተ ነገር እንዳለ እረዳለሁ፡ አያችሁ። ይህ እውነት ነው፡ ምክንያቱ፡ እሱ—ምንም… ቢያደርግ እንኳን…

105 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ከቸርች ኦፍ ክራይስት፡ አንድ ወንድም ይመጣል። እና፡ አቤት፡ ቆም አለና፡ “ይህ ሰው ሰይጣን ነው፡” አለኝ። አያችሁ? እንዲህ አለ፦ “ከመንፈስ ቅዱስ ነው ይላል’ዴ።” ቀጠለና፦ “እንዲህ ብሎ ነገር የለም። አዎን፡ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፡ ብቻ ናቸው። መ—መለኮታዊ ፈውስም ቢሆን የተሰጠው ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነበር።” እያለ ለግማሽ ሰዓት ያህል፡ ቀጠለ።

106 እኔም “ቆይ እስኪ፡ ወንድሜ። ቆይ፡ መልስ ለመስጠት እድል ትሰጠኛለህ ብዬ አስባለሁ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፦ “እናንተ እንደምትሉት መጽሐፍ ቅዱስ ከተናገረ ተናገር፡ ዝም ካለ ዝም በል ትላልችሁ።”

እርሱም “አዎን እንላለን፡” አለኝ።

107 እንዲህ አልሁት፦ “እንግዲህ፡ መንፈስ ቅዱስ የተቀበሉት አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ናቸው ብለሃል። መጽሀፍ ቅዱስ ግን፡ ‘መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ፡ አንድ መቶ ሀያ ወንዶች እና ሴቶች ነበሩ ይላል።’ እስኪ ንገረኝ፡ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ አልነበረውም እያልከኝ ነውን? ከሁሉ በኋላ ከብዙ ጊዜ በኋላ ተቀብሏልና፡ አያችሁ። ‘የፈውስ ስጦታው የተሰጠው ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ነው፡’ ደግሞ ብለሃል። እስጢፋኖስም ከጥቂት ቀናት በኋላ ወረደ፡ እርሱም ከአሥራ ሁለቱ አንዱ አልነበረም። ሰባኪ እንኳን አልነበረም። ድዲያቆን ግን ነበረ፡ ወደ ሰማርያም ወርዶ አጋንንትን አወጣ።” “ወንድሜ፡ ሆይ!” አልኩትና አሁን ጸጥ አለ፡ አዎን፡ እንዲህ መያዝ አለብህ፡ አልኩት።

108 ካለቀ በኋላ፡ “ግን፡” “ሰይጣን ብለህ ስለጠራኸኝ ይቅርታ አድርጌልሃለሁ፡ ለማለት ፈልገህ እንዳይደለህ ገብቶኛልና፡” አልኩት።

109 ከጨረሰ በኋላ፡ ወደ'ኔ መጣና። "አንድ ማለት የምችለው ነገር አለ። ይህም የክርስቶስ መንፈስ አለህ፡" አለኝ።

110 "እንግዲህ፡ ወንድሜ፡ እኔ የትኛው ነኝ፡ ዲያብሎስ ወይስ የክርስቶስ ነኝ?" አልኩት፡ አያችሁ? አያችሁ?

111 እኔ እላችኋለሁ፡ አስተውሉ፡ ምንም ያህል፡ እየተቃረነ ቢቆይም፡ አለመስማማት ውስጥ እና ባላንጣነት ውስጥ ቢቆይም፡ ይህ ሰው፡ እንደምወደው ሊመሰክር ይችላል። እንደው...

112 እኔ ህይወቴ በሙሉ፡ ከአውሬዎች ጋር ነው፡ አዳኝ ነኝና። ሰዎችም፡ ያኔ ያንን ድብ፡ በሰለት በገደልኩት ጊዜ፡ "እንዴት... " ነው ይሉኛል፡ አያችሁ። "ድቡ አላስፈራህም?" ይላሉ፡

113 "በጭራሽ፡ አያችሁ፡ እሱን ብፈራው ኖሮ፡ ይገድለኛል፡" አልኳቸው።

114 ልታታልሏቸው፡ ግን፡ አትችሉም—አያችሁ። እንደምትፈራ፡ ወይም እንደማትፈራው ያውቃሉ። ፈረሰን ከፈራችሁት፡ ምን እንደሚያደርጋችሁ ጠብቁት፡ ይረግጣችኋል። አያችሁ? ስለዚህ ፈሪ ከሆናችሁ... ማስመሰል አትችሉም። እውነት ሊኖራችሁ ያስፈልጋል።

ከሰይጣን ጋርም እንደዛው ነው።

115 በሰዎች መካከልም ያው ነው። ሰዎችን መውደድ ያስፈልጋችኋል። ማስመሰል አይቻልም። የእውነት ይኑራችሁ፡ ካልሆነ ግን ከለራችሁ የሚገለጥበት ጊዜ ይመጣል፡ አያችሁ። ትክክል ነው። ሰዎችን በእውነት መውደድ አለባችሁ፡ እንደምትውዷቸውም ይወቁ። አያችሁ፡ ፍቅር የተለየ ነገር አለው።

116 እናም ሰውዬው አሁን፣ ከጥቂት ቀናት በፊት ደውሎ፡ ባለቤቴን፦ "ወንድም ብራንሃምን ማግኘት እችላለሁን?" አላት፡

"የለም፡" አለችው።

117 "ደህና፡ ይህ ለማለት ፈልጌ ነው። ከሱ ጋር፡ በቲኦሎጂ አልስማማም፡ ይሁን እንጂ የክርስቶስ ባርያ መሆኑን እመሰክራለሁ፡" አላት።

118 እንግዲህ፡ ከዚያ በኋላ፡ ከመውጣቴ በፊት፡ ደብዳቤ ላከልኝና፡ እንዲህ አለኝ፦ "አንተ ሰትመለስ፡ ወድያው እመጣለሁ። አንተ የምትለው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መጠመቅ እፈልጋለሁ አለኝ።"

119 እና፡ እንዳያችሁት፡ እንዲህ ለማለት፡ ቢሰማችሁ... እንዲህ ለማለት ቢሰማኝ፦ "ተው ባክህ፡ ዝም ብላችሁ ናችሁ። የሐይማኖት ተቋማችሁ አይረባም፡ የቸርች ኦፍ ክራይስት ሰዎች ሁላችሁ—አትረቡም። አርባና ቢሶች ናችሁ። አጋንንቶች—ናችሁ።" ብለው ኖሮ ገንዘቤ ባላደረኩት ነበር። መውደዴ ከልቤ ሳይሆን፡ እንደምወደው ብነግረው ኖሮም፡ በደንብ ያውቅ ነበር። እውነቱ ይህ ነው። ከልባችሁ ሊሆን ይገባል።

120 በመለየት ጸጋ፡ መድረክ ላይ በምወጣባቸው ምሽቶች ላይ፡ አያችሁ። በፍጹም አልበላም። ምንም አላሰበውም፡ ከአራት ሰዓት ጀምሬ፡ እጾማለሁ እጸልያለሁ፡ በጓዳዬ እቆያለሁ። እንደሚያደርግልኝ፡ ራሱ ቃል ገብቶልኛልና። እኔ አደርግልሃለሁ ብሎኛልና ቃል ገብቶልኛልና፡ ያለ እንዳች ጥርጣሬ እሄዳለሁ።

ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ አሳ... ቤ (ምን? ) እንደሆነ፣ ግቤ (ምን? ) እንደሆነ አውቃለሁ፡ ይህም ለእግዚአብሔር መንግሥት መሰፋት ነው።

121 ሰው **በዚህ** መንገድ፣ **በዚያ** መንገድ ቢሄድ፣ የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ቢሄድ፤ ወደ ክርስቶስ እስከመጣ ድረስ፡ ለእኔ ምንም ችግር የለውም። ይህን ከልቤ ነው። አያችሁ? ምንም ይሁን፡ ወደ ቸርች ኦፍ ክራይስት ሄደን ብንቀላቀል፡ ምንም ችግር የለውም። ጥሩ ነው። እሱ... የትኛውን ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀላል፡ ለእኔ አያስጨንቀኝም። ዋናው ነገር፡ ነፍሱን ለክርስቶስ ማሸነፍ መቻል ነው።

122 ስለዚህ አልኩት፡- "ወንድም ኔስ፡ ልዩ ለመሆን አይደለም አልኩት... " አሁን እንዲህ አደርጋለሁ... "ይህን ማለት እና ማስረዳት እፈልጋለሁ፡" አልኳቸው። **ይህን** ብጠቀምበት ችግር አለው'ዴ ወንድሜ? [እሱም "ትችላለህ፡" አለ።—አርታዒ።] እናም፡ በዚህ ውስጥ፡ እዚህ ላላችሁ ወንድሞች እንዲህ እላችኋለሁ። ይህ ነገር፡ በየሐይማኖት ተቋሞቻችሁ ውስጥ አልናገረውም። ከፈቀዳችሁልኝ፡ እና ከተባበራችሁኝ፡ እንደው—እንደው—ወንድማችሁ ልሁንና። አያችሁ? እኔ፡ እንደው—ከተሳሳትኩ፡ ይቅር በሉኝ። ዛሬ ጠዋት ከሁለቱም ጎራዎች እዚህ ተቀምጣችሁ ስላላችሁ፡ ላብራራላችሁ እፈልጋለሁ፡ ሁለቱም ዋንነሶች፡ እና—እሴምብሊዎች፡ እንዲሁም የሰላሴ እምነት ተከታዮች እዚህ አሉ።

123 አሁን ይህን አሳብ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። አንዳቸው ከሌላው ጋር እስከተጨቃጨቁ ድረስ፡ የልባቸው አሳብ ስህተት ስለሆነ፡ ሁለቱም ወገኖች ተሳስተዋል ለማለት እፈልጋለሁ። ግባችሁ ምንም ይሁን፡ አሳባችሁ እስከተበላሸ ድረስ፡ የግባችሁ አሳብ የተበላሸ ስለሆነ፡ በፍጹም አይሰራም። ይህ እውነት ነው።

124 አንዳንድ ሰዎች፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አንተ'ኮ ኦንሊ ጂሰስ ነህ፡" ይሉኛል። ይህ ስሕተት ነው ማለት እፈልጋለሁ። እኔ ኦንሊ ጂሰስ አይደለሁም።

125 ሌሎችም "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የሥላሴ አማኝ ነህን፡" ይሉኛል? አይደለሁም፡ ጌታዬ። የሥላሴ አማኝ አይደለሁም። እኔ ክርስትያን ነኝ። አያችሁ? እ—እ—አይደለሁም... የሥላሴ አማኝ "ሰላሴ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳን፡ ቃሉ አልተጠቀሰም። እና ሦስት ራሳቸውን የቻሉ አማልክት አሉ ብዬ አላምንም።

126 ሦስት መገለጫዎች ያሉት አንድ አምላክ እንደሆነ አምናለሁ፡ ይህም አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው። ለዚህም ነው በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቅ የታዘዝነው። ይህም እግዚአብሔር ወደኛ መምጣቱ፡ መውረዱ እንደሆነ አምናለሁ።

127 እግዚአብሄር፡ ለመጀመርያ ጊዜ፡ ለሰዎች የታየው፡ በእሳት አምድ አምሳል ነው። ይህን ታምናላችሁ፡ አይደል? ይህም... መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ማንም ሰው በምድረ በዳ የነበረው የእሳት አምድ ሌጎስ እንደነበረ ይረዳል፡ ያም የቃል ኪዳኑ መልአክ ነው፡ እርሱም ክርስቶስ ነበረ።

128 ምክንያቱም፡ እሱ እንዳለው... እሱ... ቆይ... በቅዱስ ዮሐንስ 6 ይመስለኛል፡ "ከአብርሃም በፊት፣" **"እኔ ነኝ፡"** ብሏል። እሱ **"እኔ ነኝ"** እንደነበረ ተናግሯል።

129 ስለዚህ፡ ሰው ተራራውን ቢነካ፡ እስኪገደል ድረስ፡ ያ አምላክ፡ ቅዱስ ነበረ፡ አያችሁ። በጣም ጥሩ። አሁን፡ ይህ አምላክ ራሱ በፈጠራቸው ፍጥረት መካከል እራሱን መልሶ ማቅረብ ፈለገ። እንግዲህ፡ ኃጢአተኞች ስለ ነበሩ፡ የፍየሎች እና የበጎች ደም ኃጢአትን ከቶ ስለማያስወግዱ፡ ሊቀርባቸው አልቻለም። ያንን እናውቃለን። ኃጢአትን ብቻ ይሸፍናልና።

130 እንግዲህ፡ ያን የእሳት ዓምድ የሆነው አምላክ፡ በልጁ በኩል፡ ሥጋ ሆነ፡ እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚባል ሥጋ ውስጥ አደረ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ “በእርሱም የመለኮት ሙላት በሰውነት ተገልጦ ይኖራል።” ኢየሱስም፡ በ... በአንደኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ፡ “ያለ ጥርጥር፡ እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ታላቅ ነው” ይላል። እነሱ ታላቅ ከተባለ፡ እኛስ፡ ምን አደርግን፡ አያችሁ? “እግዚአብሔር በሥጋ ስለተገለጠ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር ታላቅ ነው፡ ለመላእክት የታየ፡ ወደ ክብር ያረገ፡” ወዘተ። እና፡ በቅዱስ ዮሐንስ 14 ላይ፡ ለቶማስ፣ “እኔን ስታየኝ፡ አብን አይተሃል። ለምንስ ‘አብን አሳየን፡’ ትላለህ? ” መጽሐፍ ቅዱስም፦ “እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ፡ አለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር፡” ይላልና።

131 እንግዲህ አሁን፡ እግዚአብሔር ሦስት ሰው፡ ሦስት አምላክ ሊሆን አይችልም። በአንድነትም፡ ኢየሱስ የራሱ አባት ሊሆን አይችልም። አያችሁ? ስለዚህ፡ አያችሁ፡ ሁለቱንም በጥልቀት ስህተት ያደርጋቸዋል።

132 እንግዲህ አሁን፡ ካስተዋላችሁ፡ እንዲህ የሚል ነገር የለም... ሦስት አማልክት አሉ ካልን፡ አረማውያን ነን። ይህን፡ እናውቃለን።

133 አንድ ቀን፡ ከአንድ አይሁዳዊው ጋር እየተነጋገርኩ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አምላክህ የትኛው ነው? አምላክህ፡ አባት ነው፣ ልጅ ነው፣ ወይስ መንፈስ ቅዱስ? የአንተ የትኛው ነው? ”

“ምነው፡ ሦስት አምላክ’ኮ የለም፡” አልኩት።

134 “እግዚአብሄርን በሦስት ቆርጣችሁ—ቆራርጣችሁ ለአይሁድ መስጠት አትችሉም፡” አለኝ።

እኔም አዎን፦ “አይቻልም፡ ጌታዬ።” አልኩት...

135 ጆን ራይን፡ በፎርት ዋይን ከዓይነ ስውርነት ተፈውሶ በነበረበት ጊዜ፡ ትዝ ይላችኋል፤ በሚሺዋ-... ወይም በፎርት... ቤንተን ሃርቦር የሚኖር አንድ ራባይ ነበረ። “እግዚአብሄርን ለሦስት ቆራርጣችሁ ለአይሁድ መስጠት አትችሉም፡” አለኝ።

136 “በጭራሽ አይቻልም። እኔም አላደርገውም፡” አልኩት። “ራባይ ሆይ፡ ነብያትን ማመን ይከብድሃልን? ” አልኩት፤

“አይከብደኝም፡” አለኝ።

137 አልሁት፦ “ኢሳይያስ 9:6፡ ስለ ማን ይናገራል፡ ‘ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል፣ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የሰላም አለቃ ይባላል ያለው ለማን ነው’? ”

“ለመሲሑ ነው፡” አለኝ።

“እሺ፡ ራባይ፡ መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግኑኝነት ምንድነው፡” አልኩት?

“ራሱ እግዚአብሔር ነው፡” አለኝ።

138 “የእኔም አሳብ ይህ ነው።” አየህ? እንግዲህ አሁን፡ ይህ፡ እውነት ነው። እሱ እንደዛው ነውና። በል አሁን፡ “ነብይው ከተናገራቸው ሁሉ ኢየሱስ ሳይፈጽም ያለፋቸው ነገሮች ንገረኝ” አልኩት። ማልቀስ ጀመረና ተንጎራደደ። “ጃን ራይን፡ ዓይኑ የተከፈተው በዚህ ነው፡” አልኩት። አየህ?

እርሱም “እግዚአብሔር ልጅ ወልደዋል መባል ከሱ ይራቅ!” አለ፤

139 እንዲህ አልኩት፦ “ነብዩ እንዲህ ይሆናል እንዳለው፡ ታላቁ ጀሆቫ አንድ ሴት ላይ ጸለለ፡ የደም ሕዋስ ፈጠረ። ከዛ የደም ሕዋስ የክርስቶስ አካል መጣ።

140 “ራባይ ሆይ፡ በብሉይ ኪዳን፡ ተመልከት፡” እንዲህ አልኩት፦ “ሰው መስዋዕትን ሊሠዋ ሲሄው፡ የበግ ጠቦት ይወስዳል። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንደጣሰ አውቆ ጠቦት ይወስዳል። ኃጢአቱን ይናዘዛል፡ ጠቦቱ ይገደላል። እጆቹ በበጉ ላይ አድርጎ ንሰሓ ሲገባ ሳለ... በኃጢአቱ ምክንያት እሱ ራሱ መሞት እንደነበረበት ያውቃል፡ በፈንታው ግን ጠቦቱ ሰፍራውን ይወስድለታል። የደም ህዋሱ ይፈሳል፡ የጠቦቱ ትንሿ ህይወት እስክትዝለፈልፍ ድረስ፡ እስክትወጣ ድረስ፡ ታናሹን ጠቦት በእጁ ይይዘዋል። ከዚያም ካህኑ፡ ደሙን፡ የፍርድ የናስ መሰውያ ላይ፡ በእሳቱ—ላይ ይረጨዋል።”

141 ከዚያም አልኩት፦ “ያ ሰው፡ በሱ ፋንታ በጉ ሰፍራውን እንደወሰደለት አውቆ፡ ከዚያ ይሄዳል፡ ሲመለስ ግን፡ በመጣ ጊዜ ይዟቸው የመጣውን ምኞቶች ሁሉ ይዞ ይመለሳል፡ ምክንያቱ፡ ሐጢአት ሊያሰወግድ ስለማይችል ነው። አየህ? አሁን፡ እንግዲህ፡ በዚህ ጉዳይ ግን፡ ‘መስዋዕት አቅራቢው፡ አንዴ ከነጻ በኋላ የሐጢአት ሕሊና የለውም።’ እዚያም በየዓመቱ የሚቀርብ መባ ነበር። አሁን ግን፡” አልኩት፡ “አሁን እንዲህ አይነት ጊዜ ነው፡ ‘መስዋዕት የሚያቀርበው አንዴ ከነጻ በኋላ የኃጢአት ሕሊና አይኖረውም።’ ምክንያቱ...

142 “ይህውልህ፡ ራባይ። በሄሞግለቢን ውስጥ፡ ከሴል የሚነሣው ትንሹ ህይወት፡ ከወንዱ ይመነጭና፡ ወደ ሴቷ ይገባል። እሷም እንቁላሉን ታዘጋጃለች፤ ዶሮም እንቁላል ልትጥል ትችላለች፡ ከወንዱ ወፍ ጋር ካልሆነ ግን፡ በጭራሽ አይፈለፈፍም።”

143 እኔም አልኩት፡ “ስለዚህ ጊዜንና ሰማያትን የሞላ፡ ልዑል እግዚአብሄር፡ አንዲት ትንሽ ዘረ መል ሆኖ እስከ ሴት ማህፀን ድረስ ወረደ።” ከዛ እንዲህ አልኩት፡ “ዛሬ እኛ በዳንን ጊዜም... ኢየሱስ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ አይደለም፡ ከእንቁላል ሥጋ ብቻ ነውና። ሕይወቱን የያዘ ግን ደም ነው። ስለዚህ—መጽሐፍ ቅዱሰ... ሰለ እኛ ‘የዳንነው በእግዚአብሔር ደም ነው፡’ ይላል። አየህ፡ አምላክ ነበረ እንጂ፡ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ አልነበረም። ስለዚህ፡ ወደ መሠዊያው፡ በእምነት ቀርበን፡ እጃችንን በራሱ ላይ እንጭናለን፣ በቀራንዮ የነበረው እንባ እና ሰቃይ ይሰማናል፣ እሱ እንደሞተልን፡ እኛም እንዳጠፋን አምነን፡ ሐጢአታችንን እናንዘዛለን!

144 “ስለዚህ አየህ፡” አልኩት፡ “የጠቦቱ ደም በዚሁ ላይ ሊመጣ አይችልም፡ ያ ደም... ህዋሱ ይፈሳል፡ በውስጡ የነበረው ህይወት ይወጣል፡ የበጉ የደም

ህዋስ ቢፈስም፡ የእንስሳ ህይወት ስለሆነ፡ ከሰው ህይወት ጋር ስለማጣጣም፡ መስዋዕት ወደሚያቀርበው ሰው አይመጣም።

145 "አሁን በዚህ ዘመን ግን፡ ያ የደም ህዋስ በፈሰሰ ጊዜ፡ የሰው ደም አልነበረም። የመጣልን፡ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። እና መስዋዕት የሚያቀርበው ሰው፡ በእምነት፡ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ እጁን ጭኖ ኃጢአቱን ሲናዘዝ፡ የሌላ ሰው ሕይወት ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ሕይወት፡ የዘላለም ሕይወት ወደ ሰውዬው ይወርዳል። **ዞዊ** የሚለው ቃል፡ ሲተረጎም 'የእግዚአብሔር ሕይወት' ማለት ነው። ዞዊ እሰጣችኋለሁ፡ ዘለአለማዊ ህይወት እሰጣችኋለሁ ብሎናልና፡ እነሆ አሁን የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ሆነናል። ይኸው ነው።"

146 እንዲህ አልኩት "ይህ ማን ነው? ከላይ የወረደ እግዚአብሔር ነው። መጀመርያ፡ መጣ፡ 'አንድም ሰው ሊነካው አልቻለም ነበር።' ከዚያም 'ኃጢአትን ለመቅመስ... ኃጢአትን ለመውሰድ፡' በአካል ወረደ። አየህ፡ እግዚአብሄር፡ ጻድቅ ይሆን ዘንድ፡ ሊያደርገው የሚችለው ብቸኛው መንገድ፡ በዚህ መልኩ በማድረግ ነው።"

147 ለምሳሌ፡ እግዚአብሔር በሰው ዘር ሁሉ ላይ እንዳለው ስልጣን፡ ዛሬ ጠዋት በዚህ ጉባኤ ላይ እኔ የበላይ ብሆን፡ እና "ይሄን አምድ ቀድሞ የሚያይ ሰው ይሞታል፡" ካልኳችሁ፡ እና ቶሚ ሂክስ ከሁሉ ቀድሞ ቢያየው? አሁን፡ ለምሳሌ ካርልን ወሰጄ-... "ወንድም ካርልስን፣ ስለ እሱ ሙትለት" ካልኩት። ፍትሓዊነት ሊሆን አይችልም። "ሊዮ፡ ጸሐፊዬ ነህና፡ አንተ ሙትለት፡" ብላቸው። ያ ፍትህ አይደለም። "ቢሊ ፖል፡ ልጄ፡ አንተ ሙትለት።" ፍትሐዊነት አይደለም። እኔ ፍትሃዊ መሆን የምችለው፡ የእሱን ቦታ ራሴ ሰወስድለት ብቻ ነው።

148 እግዚአብሔርም ያደረገው ይህንኑ ነው። እርሱም፡ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው። ፈጠረውም... ራሱ፡ ተውኔቱን ለወጠ። ለሰዎች፡ ስለ ህጻኑ ጀሆቫ ማሰብ፡ እጅግ የሚከብድ ይሆንባቸዋል። አድጎ በሳል-ሰው ሆኖ፡ መምጣት ይችል ነበር፡ እሱ ግን የፋንድያ ክምር ወዳለበት፡ ግርግም መጣ። እንደ ትንሽ ልጅ የሚያለቅስ፡ ህጻኑ ጀሆቫ። እንደ ልጅ የሚጫወት፡ ህጻን ጀሆቫ። እንደ አናጢ ሰው፡ የሚሰራ፡ ህጻኑ ጀሆቫ። የአሥራዎቹ ዕድሜ አፍላ፡ ታዳጊው ጀሆቫ። በሚንገዳገዱ ሰካራሞችና ወታደሮች ፊቱ ላይ የተተፋበት፡ በሰማይና በምድር መካከል የተንጠለጠለ፡ ጀሆቫ። ለልጆቹ የሚሞት፡ ጀሆቫ። ቤዛ ይሆን ዘንድ፡ ጀሆቫ፡ ሞተ፡ ሌላ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነው! እያችሁ፡ ያ፡ የእግዚአብሔር ስራ ነበር። ለምን? ወደ ሰዎች ልብ ለመመለስ እየሰራ ነበረ።

149 ያኔ፡ **በዚያ** ሁኔታ ሳለ፡ እሱን መንካት አይቻለንም ነበር። **እዚህ** ግን፡ በእጆቻችን ዳሰስነው። እንግዲህ ሥጋውን መሥዋዕት በማድረጉ፡ ምን አደረገ? ጀሆቫ በእኛ **ውስጥ** የሚኖር ሆነ። እኛም ብልቶቹ ነን። በጴንጠቆስጤ ቀን፡ የእሳቱ አምድ ፈነዳ፣ በእያንዳንዱም ላይ፡ የእሳት ልሳን ሆኖ አረፈባቸው፡ ይህም እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ መካከል እራሱን ቆራርሶ እንደሰጠ ያሳያል።

150 እንግዲያውስ፡ ወንድሞች ሆይ፡ አንድ ላይ መሰብሰብ ከቻልን፡ እና ያንን ወደ አንድነት ካመጣነው! አንድ ላይ ሰንሰበሰብ፡ ጀሆቫን በሙላት እናገኘዋለን። ታዲያ እንዴት ሊሆን ይችላል፡ **ይሄኛው** ልሳን ሲናገር ሲጠመቅ፡ **ይሄኛው**፡

**በዚህ** ደግሞ የሚፈሰውን እሳት ሲጠብቅ፡ ደግሞ **ይሄኛውስ**? ወደ አንድነት እናምጣው።

151 እግዚአብሔር፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን በወረደ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል፡ “በሁሉም ላይ የእሳት ልሳኖች ተከፋፍሎ ወረደባቸው።” በሁሉም ላይ... “ልሳኖች፡ እንደ እሳት፡” ፈሰሰ። እኛ ወንድማማች እንሆን ዘንድ፡ ያኔ እራሱን እየቆራረሰ፡ በህዝቡ ዘንድ፡ የወረደው ያ የእሳቱ ዓምድ ነው። “እኔ በአባት እንዳለሁ አባትም በእኔ እንዳለ፡ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፡ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።” እኛ፡ አንድ፡ ነን። አንድ ነን እንጂ፡ የተከፋፈልን አይደለንም።

152 እንግዲህ፡ ጆሆቫ አምላክ፡ **ከላይ** ሆኖ፡ ከቅድስና ሕጉ የተነሣ፡ የሰውን ዘር መገናኘት ስላልቻለ፤ ጆሆቫ አምላክ ስለ እኛ ሐጢአት ሆነ፡ ዋጋም ከፈለልን፡ ይህም ጆሆቫ አምላክ ራሱ ወደ እኛ መጥቶ **በውስጣችን** ይኖር ዘንድ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ **በላይ፡** እግዚአብሔር ከእኛ **ጋር፡** እግዚአብሔር በእኛ **ውስጥ**። አንድ አምላክ እንጂ፡ ሦስት አማልክት አይደለም! ይሄን ለማወቅ ሲሞክሩ፡ ብዙ ፕሮፌሰሮች አብደዋል። መገለጥ—ነውና። ሊገለጥላችሁ ይገባል።

153 እንግዲህ፡ አሁን፣ ወደ ጥምቀት ጉዳይ ስንመጣ፡ አሁን፡ ብዙ ሰዎች... አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ መጠመቅ አለባችሁ። ወይም፡ እንዲህ ከሆናችሁ... እና—ክርክሩ ተነሣና፡ ለወንድም ሲዝም እና ለወንድም ኔስ እንደነገርኳቸው ነው። እዚህ ያላችሁ፡ ብዙዎቻቹ ምሁራን ከእኔ ይልቅ፡ እጅግ ትበልጣላችሁ፡ ነገር ግን እኔ በጉዳዩ ላይ ብዙ ጥናት አድርጌያለሁ። **የቅድመ-ኒቂያ አባቶችን፣** እና **የኒቂያውን ጉባኤ** እና ብዙ ታሪክ ተመራማሪዎችን፡ እና የመሳሰሉትን አንብቤያለሁ።

154 ይህ ጉዳይ በኒቂያ ጉባኤ ተነሥቶ ነበር። ሁለቱም ጎራዎች ወደ ዘር ወደ መሆን አመሩ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጽንፈኛ የሥላሴን ወገን ስትይዝ፣ ሌላኛው ወደ አንድነት ሄደ፡ ሁለቱም ጎራዎች ወጡ። እውነት ነው፡ ምክንያቱ የሰዎች ነገር ስለተቀላቀለበት ነው።

155 እግዚአብሔር ራሱ እንዲሠራ መፍቀድ አለባችሁ፡ ለማወቅ መሞከሩ አያስፈልገንም። ወንድማማቾች እንሁን። እኛ እንቀጥል እግዚአብሔርም የሚያደርገውን ነገር እንዲያደርግ እንፍቀድለት። እርሱ ወሰን አልባና ሁሉን የሚያውቅ ከሆነ፡ ፍጻሜውን ከመጀመሪያው ከተረዳ፡ እኛ ምን ማድረግ ይቻለናል? ዝም ብላችሁ ቀጥሉ። መንገዱ ይህ ነው። ትላንት ማታ እንዳልኩት፡ ከታላቁ ኢያሱአችን ጋር፡ እርምጃችሁን ጠብቁ።

156 አሁን ተመልከቱ፡ ይህ ምን ያህል አሰቂኝ እንደሆነ ላሳያችሁ እፈልጋለሁ... ሦስት አማልክት ካሉ። ሦስት አማልክት ካሉ፡ እንግዲያውስ ኢየሱስ የራሱ አባት ነበር-... ኢየሱስ አንድ ሆኖ፡ የራሱ አባት ሊሆን አይችልምና። እንዲሁም፡ ሶስት ካሉ፡ እንግዲያውስ በድንግልና መወለድ አልተወለደም። እስኪ ስንቶቻችሁ... ? አሁን **ይሄኛው** እግዚአብሔር አባት ነው ልበል፡ **ይህም** እግዚአብሔር ልጅ ነው፡ **ይህ** እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

157 አሁን፡ እዚህ ለተገኛችሁ ልዩ ልዩ ወንድሞች፡ ይህን አንድ ደቂቃ ተመልከቱትና ለማለት የፈለግኩትን ነጥብ ታዩልኛላችሁ። እግዚአብሔር እንዲያሳያችሁ እጸልያለሁ። አሁን፡ ሁለታችሁም አንድ ዓይነት ነገር ታምናላችሁ፡

ነገር ግን ዲያቢሎስ በመካከላችሁ ገብቶ በዚህ ጉዳይ ለያያችሁ። በትክክል አንድ አይነት ነገር ነው፡ በእግዚአብሔር እርዳታ፡ እና በእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ፡ አረጋግጥላችኋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ፡ አትቀበሉት። እውነት ነው።

158 አሁን ግን ተመልከቱ። **ይህ** (ምንድነው? ) እግዚአብሔር አባት ነው፣ **ይህ** እግዚአብሔር ልጅ ነው፣ **ይህ** እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። እሺ፡ አሁን፡ እነዚህ ሦስት ነገሮች ካነጠፍን፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል እዚህ ጋር ቆም እንበል፡ እግዚአብሔር አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ።

159 ተውት፡ ይህንን ለማድረግ ጊዜ—አይኖረኝም። እ... [ወንድሞች ሁሉ "ቀጥልበት! ቀጥልበት!" አሉ—አርታዒ።] እሺ፡ ግን፡ እያችሁ፡ በተቻለኝ ፍጥነት እፈጥናለሁ። ይቅርታ አርጉልኝ፡ ወንድሞቼ፡ ከዚህ በፊት ግን—ከእናንተ ጋር—የመናገር ጊዜ አግኝቼ አላውቅምና፡ አሁን ግን—ይህንን ማድረግ ፈልጌአለሁ።

160 እና፡ ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ። እሺ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ማን ነበረ? እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነበረ። ይሄን ሁላችንም እናምናለን። ልክ ነው? [ጉባኤው ሁሉ "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እሺ።

161 አሁን; ማቴዎስ 28:19ን ስንወስድ; ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፣ በልጅ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አላቸው፡" ከአስር ቀን በኋላ ደግሞ፡ ጴጥሮስ "ንስሓ ግቡ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡" አላቸው። የሆነ ነገሩ ላይ ቀጥተኛ ተቃርኖ አለው። አሁን፡ ዝም እንበልና... እንዲህ እናድርግ...

162 ሰው ሁሉ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡ ወዘተ። ይኸውላችሁ። ወንድሞች ሆይ፡ እምነቴ ይህ ነው፡ በፊታችሁም አስቀምጬዋለሁ። ይህን በየመሰውያው አልናገረውም፡ ከእንግዲህ የእናንተ ጉዳይ ነው። ስለዚህ እኔ ግን መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጥላችሁ፡ በሁለቱም በኩል የማየውን እይታ አሳያችኋለሁ፡ እያችሁ።

163 አሁን፣ ማቴዎስ 28:19፣ እንግዲህ—ማቴዎስ 28:19 ከሐዋርያት ሥራ 2:38 ጋር የሚቃረን ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቃርኖ ያለው ከሆነ፡ የተጻፈው ነገር ከወረቀት የዘለለ ሌላ ዋጋ አይኖረውም።

164 አሁን በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ላይ ካስተዋላችሁ ግን፡ ኢየሱስ ለጴጥሮስ፡ መገለጥን እና ቁልፎችን ሰጥቶታል።

165 አሁን፡ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሥነ መለኮት በአንዳንድ ሰው-ሰራሽ ዘዴዎች አይገለጥም። በጭራሽ። በመገለጥ ነው።

166 ከመጀመርያ ጀምሮ፡ በመገለጥ ነበረ። አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለምን አቀረበ? ፒች፣ እና አፕል፣ እና ብርቱካን፣ እና ፖም አለመሆኑ፡ "ስለተገለጠለት ነው።" አፕል፡ ሴቶች እርቃን መሆናቸው እንዲያውቁ የሚያደርግ ከሆነ'ማ፡ አሁንም ብናከፋፍላቸው ይሻለናላ ወንድሞቼ። አይመስላችሁም? እንግዲህ፡ ይህ፡ መጥፎ ንግግር ይመስላል፡ እኔም እንደዛ ለማለት ፈልጌ አይደለሁም። ነገር ግን፡ አፕል አይደለም። ኖ፡ ስር። ስለዚህ፡ እንዲህ ከሆነ፡ እንግዲያውስ፡ የአባቱ ደም እንደነበረ፦ "ለአቤል

ተገልጦለታል።" በዚህም ደም አቀረበ፡ በመገለጥ ነውና። ነገር ሁሉ የተገነባው በዚህ መሰረት ነው።

167 አሁን ተከታተሉ፡ ይህ ሰው ያልተማረ አሳ አጥማጅ፡ በቂ ትምህርት የሌለው ነበረ... ያልተማረ መሃይም ነበር ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ኢየሱስ፡ "እኔን የሰው ልጅ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? " ብሎ በጠየቀ ጊዜ፡ በዚያ ቆሞ ነበር፡

168 ሌሎች፡ "አንተ፡ እከሌ ነህ—አንተ፡ ሙሴ-... " ወይም "'አንተን፡ ሙሴ ነህ—ይሉሃል።'"

"እኔን ማን እንደሆንኩ፡ ይላሉ? "

አንዳንዶች፡ "ኤርሚያስ ነው፡ ወይም ከነብያት አንዱ፡ እና **እንዲህ፣ እንዲያ** ወይም **ሌላ** ይሉሃል።"

169 "ስለነሱ አልጠየቅኋችሁም። የጠየቅኩት **እናንተን** ነው። ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? " አላቸው፤

170 ጴጥሮስም ቀርቦ፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፡" አለው።

171 እርሱም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፡ ብፁዕ ነህ፡" አለው። አሁን ተከታተሉ። "በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም።" አያችሁ?

172 አሁን ተመልከቱ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ ቤተ ክርስቲያንን የሰራት በጴጥሮስ ላይ ነው ትላለች። ያ ስህተት ነው።

173 የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ፡ "በራሱ ላይ ሠራት፡" ትላለች። አሁን ግን ስሙና፡ እንዲህ ነውን ብላችሁ መርምሩና እወቁት።

174 የመሠረታት እሱ ማን እንደሆነ ባለው የማንነቱ መንፈሳዊ መገለጥ ላይ ነው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ፡ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፡ ብፁዕ ነህ። ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም። እኔ አንተን ስምዖን ነህ እላለሁ፡ በዚህ አለት ላይ" (የምን አለት? የመገለጥ አለት) "ቤተ ክርስቲያኔን እገነባለሁ፡ የገሀነም ደጆችም አይችሏትም።"

175 ያኔ፡ ማቴዎስ 28 ሲጠቀስ'ኮ ጴጥሮስ በቦታው ቆሞ ነበር፣ ከአስር ቀን በኋላ ግን፡ ሌላ መገለጥ ይዞ፡ "የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡" ስም መጠመቅን ይዞ ብቅ አለ። ለምን እንደዛ አደረገ? ወንድሜ፡ የእግዚአብሔር መገለጥ፡ እና የመንግሥቱ ቁልፎች ስለያዘ ነው።

176 ምናልባት አሁን ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ አንዱን ወገን ብቻ ልጎዳው እችላለሁ፡ ነገር ግን አንድ ደቂቃ ብቻ ጠብቁኝ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ሰው "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀበት አንድም ቦታ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ሰፍራ የለም። ካለ ግን፡ አውጡ። በቅዱስ ታሪክ ውስጥም ከየትኛውም ቦታ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን እስከተመሰረተችበት ጊዜ ድረስ፡ አንድም ቦታ ካገኛችሁት፡ እንድታወጡት እፈልጋለሁ። አሁንም፡ ምንም ቦታ የለም፡ ይህም እውነት ነው።

እናንተም ዋንነሶች፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ አንድ ሴኮንድ ብቻ ጠብቁኝ።

177 አሁንም፡ የትም አታገኙትም... በመጽሐፍ ቅዱስ፡ "የአባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ" አሰራር ጥቅም ላይ የዋለበትን አንድ ጽሑፍ ሊያሳየኝ የሚችል ሰው

ካለ፡ በዛ መልኩ የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ መጥታችሁ እንድትነግሩኝ ግዴታ አለባችሁ።

178 አንዳንዶች፡ "እኔ፡ ጴጥሮስ ካለው ይልቅ፡ ኢየሱስ ያለው ይሻለኛል፡" ይላሉ። እርስ በእርሳቸው፡ የሚቃረኑ ከሆነ፡ ምን ማድረግ እንችላለን? ሁለቱም እግዚአብሔር ከሌለበት፡ የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ልክ ይሆናል?

179 ሁሉም መገጣጠም እና አንድ መሆን አለበት፡ የእግዚአብሔር መገለጥ ብቻ ነው። ትምህርት ቤት በጭራሽ አያስተምሩትም። እናንተ ማየት ካለባችሁ፡ በመገለጥ ብቻ ነው።

180 ሁለቱ ሰዎች፡ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ከሆነ፡ ምን ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ እያነበብን ነው? ዮሐንስ 14 ትክክል ይሁን አይሁንስ በምን አውቃለሁ? ዮሐንስ 3 ትክክል ይሁን አይሁንስ በምን አውቃለሁ? እንዴት፣ እንዴት፣ እንዴት አውቃለሁ? አያችሁ?

181 ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ እምነት የሚኖረኝ ብቸኛው መንገድ፡ መፅሐፍ ቅዱስ ትክክል መሆኑን በማወቅ፡ ትክክል መሆኑ በማመን፡ ከእርሱም ፈቀቅ አለማለት ነው። ባይገባኝም፡ እንዲሁ፡ እቀበለዋለሁ።

182 እነዚህ ተቃርኖዎች ሲመጡብኝ ግን፡ ያን ጊዜ፡ ለመጠየቅ እግዚአብሔር ፊት እሄዳለሁ። በሰብሰባው እና በሌሊት ላይ ያገኘኝ ያው መልአክ፡ ይህን ያስተማረኝም እርሱ ነው። ገባችሁ? አሁን ተመልከቱት፡ይህ እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ።

183 አሁን፡ ማቴዎስ 28:19፡ እስቲ ለአፍታ እንመልከተው። እዚህ ጋር፡ ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 2:38 ላይ፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡" ብሎ የተናገረውን ልውሰድ። ማቴዎስ ደግሞ "አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፡" ብሏል።

184 አሁን አዳምጡ። "እያጠመቃችኋቸው፡" ባላቸው ጊዜ… "በአባት ስም፣ በልጅ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም" አላላቸውም። በፍጹም እንዲህ አላለም። "በስም ላይ… ሌላ ስም… ሌላ ስም" የለም።

185 እንዲሁም "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ **ስሞች** አጥምቋቸው፡" አላላቸውም፡ ትርጉም አይሰጥምና።

186 ያለው ግን፦ "በአባት፣ በልጅ እና፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም (N-a-m-e) አጥምቋቸው ነው።" ልክ ነው? "… በአባት፣ በልጅ እና በመንፈስ ቅዱስ፣" "በ፡ በ፡ በ፡" የሚል ማሰርያ አለው።

187 **ስሞች**፡ አላለም። ወይም "የአባት ስም፣ የልጅ ስም፣ የመንፈስ ቅዱስ ስም፣" አይደለም። "በአባት፣ በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ **ስሞች**፣" አይደለም። ነገር ግን፡ N-a-m-e፡ "በአባት፣ በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ፣" ነጠላ "ስም፡" ነው። እንግዲህ አሁን፡ በዚህ ለመጠመቅ ትክክለኛው ስም ማን ነው? ስሙ አንድ ስም ነው። የትኛው ነው? ትክክለኛው ስም "አባት" ነውን፣ ትክክለኛው ስም "ልጅ" ነውን፣ ወይስ ትክክለኛው ስም "መንፈስ ቅዱስ" ነውን?

188 የሆነ "ስም፡" ነው። ልክ ነው? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] እንግዲህ፡ አሁን አንድ ነገር፡ ልጠይቃችሁ። "በአባት፣ የልጅ፣ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፡" ብሎ ኢየሱስ ከተናገረ… እንግዲያውስ፡ ያ "ስም፡"

ኢየሱስ እንደተናገረ የምታምኑ ስንት ናችሁ? [“አሜን።”] መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ማቴዎስ 28:19፡ “የአባት፣ የልጅና... ስም”

189 [ወንድም ብራንሃም ትኩረትን የሚከፋፍል ነገር አየ—አርታዒ።] ችግር አለ´ዴ... አይ፡ ምንም የለም... እሺ፡ ጌታዬ፡ እንዲህ አሰቤ። [አንድ ወንድም፡ “ይቅርታ፡ ወንድም ብራንሃም? አለ፡”] አዎን። [“ይህን ካሴት መቀየር ፈልጌ ነው፣ እንዲያመልጥ ስላለፈለግኩ ነው።”] እሺ ይሁን። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]... ? ...

190 አሁን፡ “በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም።” አሁን ስሙኝ፡ ወንድሞቼ። “አባት” የሚባል ስም የለም፡ ምክንያቱም **አባት** ስም አይደለም። መገለጫ ነው። “ልጅ” የሚባል ስም የለም፡ **ልጅ** መገለጫ ነውና። “መንፈስ ቅዱስ” የሚባል ስም የለም። የእርሱ ምንነት ነውና።

191 አንድ ቀን ጠዋት በአገልጋዮች ቁርስ ላይ እየተናገርኩ፡ አንዲት ሴት... በርግጥ፡ ያደረገችው ከሥርዓት ውጪ ነው፡ እንደዚያ የሚያደርግ ሁሉ፡ ይረብሻል። እንዲህ አለች፦ “ይቅርታ! አንድ ደቂቃ!” “መንፈስ ቅዱስ´ኮ ስም ነው፡” አለች።

192 እኔም፦ “ማንነቱ ነው። ለምሳሌ እኔ ሰው ነኝ፡ ስሜ ግን ‘ሰው’ አይደለም።”

193 መንፈስ ቅዱስ ነው። ስሙ አይደለም። ማንነት ነው። በርግጥ፡ ሰያሜ ነው፡ ይሁን እንጂ.... ሰ—ሰ... ስም አይደለም።

194 እንግዲህ፡ “በአባት፣ በልጅና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፡” ብሎ ከተናገረ፡ እናም አባት፣ ልጅ፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ ሁሉ ስም ካልሆነ፡ ታዲያ ስሙ ማን ነው? ማን እንደሆነ እንመረምራለን።

195 አሁን፡ ተረጋግታችሁ ትንሽ ጊዜ ሰጥታችሁ ከተ—ከተ—ከተከታተላችሁ፡ ማለቴ ከጊዜአችሁ፡ ትንሽ ከቆጠባችሁ፡ ቶሎ እንደርስበታለን። አሁን ማቴዎስ 28:19ን ተመልከቱ። አሁን፡ እንዲህ አልልም...

196 ምናልባት፡ አንዳንዶች እህቶች እና ወንድሞች፡ አጋጥሟሁ ሊሆን ይችላል። አንድ ቀን መጽሐፍ እንሥታችሁ ይሆናል፡ ከዛ አዙራችሁ ስታዩት፡ እንዲህ ይላል፡ “ጆን እና ሜሪ በደስታ ኖሩ” የሚል ሊሆን ይችላል። እሺ፡ ጆን እና ሜሪ እነማን ናቸው? ማን ነው... በደስታ የኖሩ ጆን እና ሜሪ እነማን ናቸው? ጆን እና ሜሪ ማን እንደሆኑ እንቆቅልሽ ከሆነባችሁ፡ የምታውቁበት መንገድ፡ አንድ ነው፡ ሄዳችሁ መጽሐፉን ማንበብ። ልክ ነው አይደል? ወደ መጀመሪያው ተመልሳችሁ ታነቡታላችሁ፡ ጆን እና ሜሪ ማን እንደሆኑ ይነግራችኋል።

197 እሺ፡ ኢየሱስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአባት፣ በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ብሎ ከተናገረ፡” **አባትም**፣ **ልጅም**፣ ወይም **መንፈስ ቅዱስ**፣ ስም ካልሆነ፡ እና እንቆቅልሽ ከሆነብን፡ ወደ መጽሐፉ መጀመሪያ ብንመለስ ይሻለናል።

198 አሁን ወደ ማቴዎስ ምዕራፍ 1 እንመለስ፡ የዘር ሐረግ እስከሚገለጥባቸው፡ 18ኛው ቁጥር እስክንደርስ ድረስ፡ ከዚህ እንጀምራለን።

199 አሁን ተከታተሉ፡ አንድ ደቂቃ ተከታተሉ። **ይህ** በቀኝ እጄ በኩል ያለው፡ አባት ነው፡ **ይህ** በመኃል ላይ ያለው፡ ልጅ ነው፡ **ይህም** መንፈስ ቅዱስ ነው። አሁን፡ **ይህ** የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ልክ ነው? እግዚአብሔር የኢየሱስ

ክርስቶስ አባት ነው። ሁላችንም እናምናለን? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] እሺ።

200 እንግዲህ ማቴዎስ 1:18 ደግሞ እንዲህ ይላል:

**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ፡ እናቱ ማርያም... ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ፡ ሳይገናኙ... በፊት፡ የማን ልጅ ፀንሳ ተገኘች...** [ጉባኤው፡ “**የመንፈስ ቅዱስ፡**” ብሎ መለሰ።—አርታዒ።]

201 አባቱ **እግዚአብሔር** ነው ብዬ ነበር።

**ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡...** ስሙን **ኢየሱስ ይሉታል፡...**

**ባልዋ ዮሴፍም፡ ጻድቅ ሰው ሆኖ፡... በህዝብ ፊት መቀጣጫ ሊያደርጋት** ሰላልወደደ፡ **በሰውር** ግን **ሊተዋት አሰበ።**

እርሱ ግን፡ **ይህን ሲያሰብ፡ እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲህም አለው፡ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፡ እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፡ ከእርሰዋ የተፀነሰው ከማን ነውና...** [ጉባኤው፡ “**ከመንፈስ ቅዱስ፡**” ብሎ መለሰ።—አርታዒ።]

202 አባቱ እግዚአብሔር ነው ብዬ አሰቤ ነበር። አሁንስ፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነውን? [“አይደለም።”] ሊኖረው አይችልም። እንደዛ ቢሆን ኖሮ ግን፡ የተዳቀለ ልጅ ነው፡ እኛስ ምን የሚሉት ሐይማኖት በኖረን? አባት የሆነው እግዚአብሔር እና መንፈስ ቅዱስ አንዱ-መንፈስ ራሱ መሆናቸውን አምናችሁ መቀበል አለባችሁ። አዎን ነው። አዎን፡ አንዱ ራሱ-መንፈስ ነው። አሁን፡ ይሄን ጨርሰን፡ አይተነዋል።

**ልጅም ትወልዳለች፡ እርሱ ሕዝቡን** ከኃጢአታቸው **ያድናቸዋልና፡ ሰሙን ኢየሱስ** ይሉታል።

... **የተባለው ይፈጸም ዘንድ፡ ይህ** ሁሉ **ሆነ...**

203 መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀስኩ ነው። እኔ ሰቀጥል፡ አገልጋዮች ታውቃላችሁ።

በነቢይ... **ከጌታ ዘንድ፡ የተባለው...** ይፈጸም ዘንድ፡ ይህ ሁሉ፡ **ሆነ፡**

... **ድንግል** ትፀንሳለች፡ ልጅም... **ትወልዳለች፡ ሰሙንም አማኑኤል ይሉታል፡ ይህም** ትርጓሜው፡... [ጉባኤው “**እግዚአብሔር ከኛ ጋር፡**” አለ።—አርታዒ።]

204 “እግዚአብሔር ከኛ ጋር!” ልክ ነው?

205 እንግዲህ የአባት፣ የልጅ፣ እና የመንፈስ ቅዱስ ሰም ማን ይባላል? [አንድ ወንድም “እየሱስ ክርሰቶስ ነው፡” አለ።—አርታዒ።] ጥሩ ነው፡ በትክክል። ጴጥሮስ “በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም” ያጠመቀው ለዚህ ነው።

206 እኔ ግን፡ በሳሮን ጽጌሬዳ ሰም ተጠመቃችሁ፣ በሸለቆው የሊሊ አበባ፣ በንጋት ኮከብ ሰም ተጠመቃችሁ፡ ሁሉም፡ መገለጫዎች ናቸውና፡ አያሰጨንቀኝም። ልባችሁ ለእግዚአብሔር ቅን ከሆነ፡ እርሱ ልባችሁን ያውቀዋል።

207 አሁን ግን፡ አሁን፡ ያንን አብራራሁት። አሁን፡ አሁን እንዲህ አልኩት... ወንድም ሲዝም እንዲህ አለ፡ “አሁን!” እርግጥ ነው፡ ያ የዋንነስ የሚመስል ነበር፡ ስለዚህ በእይታው ትክክል ነበር።

208 አሁን “ልናገራችሁ የምፈልገው ነገር አለኝ፡” አልኋቸው። አያችሁ? “አሁን ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው፡ ሁለቱም ሰዎች ያሉት፡ አንድ ዓይነት ነገር መሆኑ ነው፡” አልኋቸው።

209 ማቴዎስ፡ “በአባት ስም፡” አለ። አይደል? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርትዒ።] እሺ። ጴጥሮስ ደግሞ “በጌታ ስም፡” አለ። የማቴዎስ ወንጌል 28:19 “በአባት ስም፡” ሲል፡ የሐዋርያት ሥራ 2:38 “በጌታ ስም፡” አለ። ዳዊት ሲናገር “**ጌታ** ጌታዬን አለው፡” ብሏል። ስለ ማን ነበር? አባት እና ጌታ አንድ ስም ነው። ዳዊት ሲናገር “**ጌታ** ጌታዬን፡ ‘በቀኜ ተቀመጥ አለው፡’” ብሏል። አያችሁ፡ “በአባት ስም ሲል፣ በጌታ ስም ነው።”

210 ማቴዎስ “በልጅ ስም፡” ሲል፡ ጴጥሮስ ደግሞ “በኢየሱስ ስም፡” አለ። ልጅ ማነው? ኢየሱስ ነው።

211 “በመንፈስ ቅዱስ ስም፡” አለ ማቴዎስ፡ ጴጥሮስም “በክርስቶስ ስም፡” አለ፡ ሎጎስ።

212 **አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፣** “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።” ለምን፡ መሆን የሚችለውን ያክል ትክክል ነው። አያችሁ?

213 ወንድም ስዝም እንዲህ አለኝ፡ ማለት፡ የዋንነሱ፡ ወንድማችን ሲዝም፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ልክ ነው፡ ግን፡” “ያ’ኮ **ይህ** ነው፡” አለኝ።

214 እኔም “**ይህ’ኮ፡** ያ ነው፡” አልኩት። እውነት ነው። አያችሁ? “ያ **ይህ** ከሆነ፣ **ይህም** ያ ነው፣ ለምንድነው የምንጨቃጨቀው? ” አልኳቸው።

215 “ወንድሞቼ፡ አሁን ልምከራችሁ፡ እኔ አንድ ሰው አጥምቄ ከሆነ፡ እንዲህ ነው... ” አልኳቸው።

216 “ለምሳሌ፡ ዶክተር ኔስ እዚህ አለ።” ቀደም ብላችሁ... እንዳችሁ፡ ዶክተር ኔስን፡ አውቀዋለሁ፡ ብላችሁኛል። አልኳቸው።

217 ችግር የለውም፡ እዚህ፡ ካሉት፡ ወንድም ሂክስ ልበል፡ እርሱም... የዶክትሬት ዲግሪ አለህ። ልክ ነኝ? እሺ።

218 እኔ አሁን፦ “ለምሳሌ ዶክተር ኔስ፡ እዚህ ቁጭ ብሎ... ” “ለምሳሌ ብፈልገው... ” እንዲህ ብለው፤ አሁን፡ አንድ ሰው ለማጥመቅ፡ ወደ ውኃ ከወሰድኩት፡ ልክ እሱ እንዳደረገው አድርጌ፡ “የስሙ መገለጫዎች እንደሆኑ አድርጌ፡” እውቅና እሰጠዋለሁ፡ አልኩት።

219 “እንግዲህ፡ የአሴምብሊስ ወንድሞች የሚጠቀሙት፡ መገለጫዎቹ ነው፣ የዋንነስ ወንድሞች የሚጠቀሙትም ስሙ ነው፡” አልኳቸው። “እንግዲህ አሁን፡ ሁለታችሁ እንደተሳሳታችሁ፡ አረጋግጥላችኋለሁ፡” አልኳቸው። መቼም እንዴት ማድረግ እንደሚገባችሁ ታውቃላችሁ... በዚህም የሚጨናነቁ ሰዎች ይኖራሉና፡ ትንሽ ዘና ለማድረግ፡ በተወሰነ መልኩ ጨዋታ አዋቂ መሆን ይገባችኋል። ስለዚህ “ሁለታችሁ እንደተሳሳታችሁ፡ እኔ ግን ትክክል እንደሆንኩ፡ ላረጋግጥላችሁ፡” አልኳቸው።

220 "ለምሳሌ ወንድም ኔሰን ማክበር ብፈልግ፡ ምን እለዋለሁ... " አልኋቸው፡

221 ወይም፡ ወይም እዚህ ያለው ወንድም ሂክሰን፡ እያችሁ። ምን እለዋለሁ፡ "ሂክስ!" ብለው፡ ደስ የሚል ይመስላችኋልን? አይልም። እሺ፡ እንዲህስ፡ "ዶክተር! አንተ፡ ዶክ! ይሄስ? እያችሁ፡ አክብሮት ይጎድለዋል፡ አይደለም'ዴ?

222 "እንዲህ ከሆነ፡" አልኳቸው፡ "አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ የምታደርጉት በዚህ መንገድ ነው፡ ገብቷችኋል። እናንተ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ወንድሞች 'በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣' ስትሉ፡ 'በሬቨረንድ ዶክተር ስም፡'" እንደ ማለት ነው።

223 "እናንተም፡ የዋንነስ ወንድሞች፡ ስታጠምቁ 'ኢየሱስ!'" ትላላችሁ አልኳቸው፤ ሌላውን አይጠቀሙበትም...

224 ኦንሊ ጂሰሶች፡ "ኢየሱስ፡" የሚል ስም ብቻ ይጠቀማሉ። ኢየሱሶች ብዙ ናቸው። እሱ ግን፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ እያችሁ። "በኢየሱስ" ስም የተጠመቁ... ብዙዎች አሉ፡ እኔ ግን እንዲህ የሚል ቃል ስለሌለ፡ በዚህ መንገድም አልሄድም። ኦሪጂናሉ አይታችሁ ተጠቀሙበት፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡" ነውና። በእርግጥ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ነው። አዎን ብዙዎች ኢየሱሶች፡ አሉና። **ክርስቶስ** ማለትም "የተቀባ" ነው።

225 አልኋቸውም፡ "እሺ፡ ወንድም ኔሰም እንዲህ ተመሳሳይ ነገር ብናገረው። 'አንተ፡ ኔስ!' ብል፡ እንዲህ ማለቴ፡ ጥሩ ይመስላችኋልን? " አልኳቸው፡ "እናንተ ዋነሶች የምትሉትም እንዲሁ ነው። እያችሁ? ለተማረው እና ዶክተር ዲግሪ ላለው ሰው፡ ይህ አክብሮት የጎደለው ቸልተኝነት አይሆንምን? ይህን ለማግኘት አጥብቆ የተማረ ከሆነ፡ ያንን መዓርግ ሊሰጠው ይገባዋል።"

226 "'አንተ፡ ዶክ!' ብለውስ፡" አልኋቸው፡ "አገልጋይ ለሆነ ሰው፡ ሌላ ሰውን በዚህ መልኩ መጥራቱ ትንሽ አይሸክክም ወይ፡" አልኋቸው? ወይም፡ "እናንተ የምትጠቀሙበት መንገድ፡ በመዓርግ ጎን ለጎን በመጥራት ነው፡" አልኋቸው።

227 እኔ ግን አልኋቸው፡- "አንድ ሰው ወደ ውኃ ሰወሰደው፡ ወደዚያ ሄጄ፡ አናግረዋለሁ፡ ስሙ ማን እንደሆነ እጠይቀዋለሁ፡ እና እምነቱን አውቃለሁ።

228 "ከዛ በኋላ እጸልያለሁ፡ እንዲህ ብዬ፡ 'አሁን፡ አባት ሆይ፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ከሰዎች ሁሉ ዘንድ ደቀ መዛሙርት አድርጉ፡... "'" ብለህ እንዳዘዝከን ወንድሞች ሆይ ይህ ኦሪጂናል እንደሆነ ታውቁታላችሁ፡ አይደል። "'"... ሰዎችን ሁሉ፡ በአባት፣ በልጅና፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡ እናንተ የተማራችሁትን ሁሉ... እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው።"'"

229 "ከዛ እንዲህ እላለሁ፡ 'በእምነትህ ኑዛዜ መሰረት፡ በተናዘዝካቸው ኃጢአቶችህ፡ እና በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለህ እምነት መሰረት፡ የተወደድክ ወንድሜ ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አጠምቅሃለሁ።'"

230 እኔ አልኳቸው፡ "የማጠምቀው በዚህ መንገድ ነው። ማዓርጎቹም ጭምር፡ ማለት አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ፡ እውቅና እሰጣለሁ። ኢየሱስ፡ ይህን የተናገረበት ምክንያትም... "

231 አሁን ተመልከቱ። ይህ—እውነት ካልሆነ፡ በገዛ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ መቃረን አለ፡ የተቃረነ ነገር አለ ማለት ነው። እስኪ ይህ የቡድን ተከታይ ወንድም

ተነሰቶ፡ “**ይሄስ** ምን ማለት ነው” ቢላችሁ... ምን ታደርጋላችሁ? ያን ጊዜ ሲነገሩኝ ምን ነበር ያሉት...

232 ያኔ፡ ያ ህንዳዊ ወንድም፡ ሬድሄድን በተገዳደረው ጊዜ፡ እንዲህ አለው፡ አሉኝ፡ “ማርቆስ 16ስ? ” ባለው ጊዜ ተንደባለለ አሉ።

233 ምንም መንደባለል አያስፈልጋችሁም። የእግዚአብሄር ቃል ነው። አጥብቃችሁ ያዙት። ጸልዩ። መገለጡን ታገኛላችሁ። የሁሉ አካሄድ አንድ ነው።

234 አያችሁ፡ ሁለቱም የሚሉት፡ ተመሳሳይ ነገር ነው፡ በመዓርጎቹም አይሁን፣ በሚሸክክ መንገድም አይሁን። “እሁን... ” አልኋቸው፡

235 እኔ እውቅና ሰጥቼዋለሁ። ሌላ አምላክ ሳይሆን፡ ራሱ አባት ነው። ሌላ አምላክ ሳይሆን ራሱ ልጅ ነው። ያው አምላክ ነው! እና... ሦስት መገለጫ ነው። እግዚአብሔር በአባትነት ዘመን፡ የአባትነቱ፡ የልጅነቱ፡ ሁሉ መጥራት ከፈለጋችሁ፡ በውስጣችን የሚኖረው ያው አምላክ፡ በግል ተውላጠ ስም፡ “እኔ፡” “ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።” “ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።” ሰለዚህ፡ አያችሁ፡ ሦስት አማልክት ሳይሆን፡ ባለ ሦስት መገለጫ ነው።

አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ እና ከዛ በኋላም በጭራሽ ተጠቅመውበት የማያውቁ ከሆነ...

236 እኔ አልተቃወምኩም። ምንም ችግር የለም። እንደው፡ አንዱ መጥቶ እኔ የተጠመቅኩት በዚህ ነው ቢል፡ የተጠመቅኩት “በሳሮን ጽጌሬዳ፣ በቆላ የሊሊ አበባ፣ በንጋት ኮከብ ነው” ኢየሱስ ክርስቶስን ግን፡ እንደ ግል አዳኜ አድርጌ አምኜዋለሁ ቢለኝ፡ “እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ! ና፡ አብረን እንሂድ!” እለዋለሁ፡ አያችሁ? ይህ እውነት ነው። ምክንያቱ፡ ልባችሁ ቅን ካልሆነ፡ ከመነሻውም፡ ቅንነት የለም። በትክክል ይህ እውነት ነው። ልባችሁ—ትክክል መሆን አለበት።

237 እና እንዲህ አልኋቸው፡ “አሁን ተመልከቱ። አሁን ወንድም ኔስን ሰላም ልለው ከፈለግኩ፡ ‘ሬቨረንድ ዶክተር ኔስ’ ብዬ መጥራት አለብኝ። ይህ በትክክል እውነት ነው። አገልጋይ ነውና። ሬቨረንድ ተብሎ መከበር አለበት። ብዙ ጥናት፡ ያጠና ሰው ነው። ዶክትሬት ዲግሪ ይዟል፡ ሰለዚህ ‘ዶክተር’ ተብሎ መጠራት አለበት። ሰሙ ‘ኔስ፡’ ቢባልም። ያ መዓረጉ ነው፡ አያችሁ። አሁን፡ ‘አንተ ኔስ! አንተ፡ ዶክ!’ ብዬ አልጠራውም፡ በጭራሽ፡ ትክክል አይደለም። ‘ሬቨርንድ ዶክተር ኔስ፡’ እለዋለሁ እንጂ።

238 “አያችሁ፡ የእኔ አጠራር ይህ ነው፡ አያችሁ፡ እርሱ ራሱ፡ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ‘ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ነው’ ሁለቱ ነው።” አያችሁ?

239 እንግዲህ “እኔ በየአብያተ ክርስቲያናቶቻችሁ ሰው ካጠመቅኩ፣ የማጠምቃቸው በዚህ መንገድ ነውና፡” አልኳቸው። “ወንድም ኔስ ሆይ፡ ትቀበለዋልህን? ” ብዬ ጠየቅኩት፡

240 “አዎን። በአባት፣ በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሰም ተጠምቋልና እቀበለዋለሁ፡” አለኝ።

“ወንድም ሲዝም ሆይ፡ አንተስ ትቀበለዋልህን? ” ብዬ ጠየቅኩት፡

“አዎን፡ በኢየሱስ ሰም ተጠምቋልና እቀበለዋለሁ፡” አለኝ።

241 እኔም፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ታዲያ ችግራችሁ ምንድነው? ለምን አትቀባበሉም፡ ለምንስ ይህ ሚስኪን ህዝብ የተጠመደባቸው እነኚህ ግድግዳዎችን ለምን አታፈርሱም... ? የዋንነሶቹም፡ ምዕመናን ሁሉ፡ በጣም ይፈልጉታል፡ ከአሴምብሊስ ጋር በህበረት ማምለክ ይፈልጋሉ። የአሴምብሊስ፡ ምዕመናን በሙሉ፡ ከዋንነሶች ጋር ማምለክ ይፈልጋሉ። ወንድማማቾች እንዲህ ናቸውና። እንዲህ ናቸው። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ እንዲጣሉ እሳክደረጋቸው ድረስ ግን... ”

242 ምን ለማለት እንደፈለግኩ አይታችኋል፡ ወንሞች ሆይ? እኔ ወደ አንድ ነገር እያመራሁ ነው፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካል አንድ ማድረግ። አላማዬም ያ ነው።

243 አሁን፡ ስለዚህ ጉዳይ አንዳች አላነሳም፡ “አንተ በኢየሱስ ስም ስላልተጠመቅክ፡ ወደ ገሃንም ትገባለህ አልልም።” ያ፡ ከንቱነት ነው።

244 በቀደም የሆነውን ነገር ላጫውታችሁ። ቴክሳስ ነበርኩና። ከዛ ከመውጣቴ በፊት... እዚህ ያሉ——ወንድሞች ምስክር ናቸው። ስፖንሰር ያደረጉኝ፡ ሰባ-ሁለት የሚሆኑ የዋንነስ አብያተ ክርስትያናት ናቸው። እና ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ የሆነው ወንድም፡ ወንድም ፔቲን፡ በዛው ምሽት ወደ መድረክ ይዤው ወጣሁ። እውነት እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ። ወንድም ፔቲን፡ የምታውቁት ከሆናችሁ፡ ከቤሞንት፡ ቴክሳስ፡ እጅግ የሚደንቅ ወንድም ነው። እስካሁን ካየኋቸው ምርጥ ሰዎች አንዱ ነው። ሚስቱ የተለወጠች ካቶሊክ ነች፡ እውነተኛ ቅድስት ሴት ነች። እሱም እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነው።

245 እስኪ ከአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ከሮይ ዊድ፡ የተሻለ ሰው ካለ ንገሩኝ። እዚህ አካባቢ ከሚታዩኝ፡ ከማውቃቸው ወንድሞች መካከል፡ አንዱን ጥቀሱልኝ። እዚህ ካለው የፊላደልፊያው ቤተ ክርስቲያን፡ እና ከሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ሰዎች፡ የተሻለ ሰው ምን ነው? የት አለ ንገሩኝ። ከጃክ ሞር የተሻለ ሰው ንገሩኝ? እስኪ ንገሩኝ። እሱ የእኛ ነው... የሚሉት ሰው ነው። አክራሪ አይደለም። አክራሪ ሰዎች ግን በሁለቱም ጎራዎች ታገኛላችሁ፡ ሰዎች የሚጠቁሙት እዛ ላይ ነው፡ ዲያብሎስም የሚጠቁመው እዚያ ላይ ነው።

246 ሁሉም ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን የሰጣቸው ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ፀጋ ባይሆን ኖሮ፡ ሁላችንም በትዕቢቶቻችን እና በነገሮቻችን እንጠፋ ነበር። በትክክል ይህ እውነት ነው። የእግዚአብሄር ፀጋ ግን አንድ ያደርገናል። “በክርስቲያናዊ ፍቅር ልባችንን ያሰረ ማሰሪያ የተባረከ ይሁን፡” ብለን መዘመራችን አይደንቅም። እንግዲህ፡ እኛ የምንፈልገው ያ ነው።

247 እና ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የቤተ ክርስትያኒቱ የበላይ ተቆጣጣሪ—— ጠራኝና፡ እንዲህ አለኝ፡ ሁለተኛ ቀኔ ነበርና። “ትናንት ማታ ያደረግከውን ግን አውቀኸዋልን? ”

“ምንድነው? ” አልኩት፡ “በጣም ድንቅ ጊዜ ነበረን፡” አልኩት።

“በመድረክ ላይ ከአንተ ጋር ኃጢአተኛ ሰው ይዘህ ነበር፡” አለኝ።

... ማን ነው እሱ፡ “እኔ አላየሁትም” አልኩት።

“ያ፡ አቶ ፔቲ፡” አለኝ።

248 “ኦህ፡” “ምን? ኃጢአተኛ?” አልኩት፡ “ወንድሜ፡ እሱ’ኮ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ሰባኪ ነው፡” አልኩት።

249 “አዎን፡ ግን አሁንም በትክክል ስላልተጠመቀ፡ ኃጢአተኛ ነው፡” አለኝ።

250 እኔም አልኩት፡ “ወንድም ፕረይ፡ እስኪ ንገረኝ።” “መንፈስ ቅዱስ ለምን ተሞላ ንገረኝ፡” አልኩት።

251 እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ጴጥሮስ ያዘዘው ምንድነው? ‘ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።’ ስለዚህ በኢየሱስ ስም እስክትጠመቅ ድረስ ኃጢአትህ አይሰረይም።”

“ፎርሙላው ያ ነው ወንድሜ?” አልኩት፡

“ፎርሙላው ያ ነው፡” አለኝ።

252 እኔም “እንግዲያውስ እግዚአብሔር፡ በሐዋርያት ስራ 10:49 ላይ፡ የገዛ ዓላማውን አፈረሰ፡ ‘ጴጥሮስ ይህን ቃል ገና ሲናገር፡ ቃሉን በሰሙት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፡’ ይላልና፡ እነዚህ ሁሉ፡ ከቶ አልተጠመቁም ነበር፡ አየህ። እግዚአብሔር፡ ገና ላልተለወጡ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን አልሰጣቸውምን?” “አሁን አንተ በየትኛው አለም ላይ ልትቆም ነው?” አልኩት፤

253 “ምን እንደምናደርግ ታውቃለህ?” አለኝ፤ “ትንሽ ክብ ድንበር አሰምረን፡ ከክቡ አንተን እናስወጣሃለን፡” አለኝ።

254 “እንዲያ ከሆነ፡” “እኔም ሌላ ክብ ድንበር አሰምሬ፡ አንተን እንደገና ወደ ውስጥ እመልስሃለሁ፡” አልኩት። “እኔ እናንተን ስለምወዳችሁ፡ አንተ ልታወጣኝ አትችልም። አየህ፡ እንዲህ ማድረግ አትችልም፡” አልኩት። “ከእናንተ ወንድሞች—መካከል እኔን የሚወዱኝ እኔን የሚያምኑኝ እጅግ ብዙ ሰዎች አሉ፡” አልኩት። “እናንተን፡ እ—እ… እንዲሁ፡ ይመጣሉ፡” አልኩት። “ይመጣሉ። አንተ ልታስወጣኝ አትችልም። አንተ ብታስወጣኝም፡ እኔ ወደ ውስጥ እመልስሃለሁ፡” አልኩት። “አንተ አንድ ድንበር ስትሰራ፡ እግዚአብሄር፡ በፀጋው፡ ሌላውን እንድሰል ያደርገኛል አንተንም እንድመልስህ ያደርገኛል፡” አልኩት። ትክክል ነው፡ እንደገና ስላችሁ ሳቧቸው።

255 እና ወንድም ሆይ፣ በክርስቶስ ስም ይህን ልበል። እኔ—የያዝኩት… ጊዜ እንደወሰድኩባችሁ ይገባኛል፡ ይመስለኛል፡ የመዝጊያ ጊዜም ደርሷል፡ ይሁን እንጂ፡ ይሄን ልበላችሁ።

256 ለዚያም ሰው፡ እንዲህ አልኩት፡ “ፍቅር እስካለህ ድረስ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እስከሰበክህ ድረስ አብሬህ እጓዛለሁ፡ ሰዎችን እሰብካለሁ—አጠምቃለሁ… የምትለውን… የኦንሊ ጂሰስ ‘በኢየሱስ፡’ ስም ጥምቀት ግን አይሁን። አይደለም፡ ጌታዬ። ኢየሱስ የተባሉ ብዙዎች ሰዎች አውቃለሁና፡ በዚያ መንገድ በእውነት—አልሄድም፤ በአፍሪካ እና በተለያዩ ቦታዎች፣ ኢየሱስ የሚባሉ ብዙ ሰዎች አውቃለሁ። ነገር ግን ‘የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ’ ቃል የምትጠቀም ከሆነ ግን፡ ከአንተ ጋር እጓዛለሁ። ምንም ችግር የለውም። እጠጋሃለሁ። ይሄን ነገር በትክክል እንድትረዳው፡ ‘አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ፡’ ማስቀደም ያለብህ ይመስለኛል።” “ማስቀደም አለብህ ብዬ አስባለሁ፡” አልኩት።

እርሱ ግን “ኦህ፡ አይሆንም፡ አይሆንም! ያ’ማ፡ ወደ ሥላሴ መመለስ ነው፡” አለኝ።

“አንዱ አምላክ በሦስት መገለጫ ነው እንጂ፡ ሥላሴ አይደለም።” አልኩት።

257 ሦስት አምላክ፡ ሦስትነት አይደለም። ሶስት አምላክ የለንምና። በእርግጠኝነት አይደለም። እንደዚህ ያለ ነገር የለምና። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። አንድ ብቻውን እግዚአብሔር አለና። “እስራኤል ሆይ ስማ፡ እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነኝ።” አንድ አምላክ! የመጀመሪያ ትእዛዝ፡ “ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ነው።” በትክክል፡ አንድ አምላክ ነው፡ ሦስት አይደለም።

258 ያ’ማ የካቶሊክ መንገድ ነው፡ ይህም፡ ከካቶሊክ ወደ ሉተራኖች ዘለቀ፡ ከዚያም ወርዶ፡ ወደ ሌሎች ደረሰ፡ እና አሁን በአጠቃላይ በሰዎች መካከል ዛሬ ሶስት አማልክት እንዳለ ይታመናል።

259 ይህ ወንጌል መቼም ቢሆን ወደ አይሁዶች... የማታደርሱበት ምክንያት በዚህ ነው... በቀደም ጠዋት ለአንድ የአይሁድ ሚሽነሪ ትንቢት፡ ተናግሬአለሁ። ለአይሁዳዊ የሥላሴን አምላክነት በፍጹም ማቀበል አትችሉም። መቼም አትችሉም። ምክንያቱ፡ ከዛ በተሻለ መልኩ፡ የተሻለ ግንዛቤ አለው። አያችሁ፡ ከዛ በተሻለ ሁኔታ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያውቃል። እግዚአብሔር፡ ለአይሁድ ሦስታዊ—አምላክ ሆኖበት አያውቅም። ያንኑ ጀሆቫ ነው ብላችሁ ማሳየት ከፈለጋችሁ፡ አሁኑኑ ይቀበለዋል። አዎን! እንዲያ ነው፡ አያችሁ።

260 እኔም ይህን ሁሉ አምናለሁ። ዮሴፍ እንዳላቸው፡ “ወንድሞች ሆይ፡ በራሳችሁ ላይ አትዘኑ፡ እግዚአብሔር ይህን አድርጎአልና፡” አያችሁ። ምክንያቱ—ይህ ሁሉ የሆነው... እስከአሁን ዘመን ድረስ ይቆይ ዘንድ ነው፡ ምክንያቱ የአሕዛብ ዘመን ማለቂያ ነውና። አሁን፡ ያንን በሙሉ ልባችን አምነዋለሁ። አያችሁትን፡ ወንድሞቼ? የሆነ ነገር ለማስረዳት እየሞከርኩ ነው፡ ይህም፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያላቸው፡ እነዚያ ሰዎች።

261 የእነ ኤሚ ማክፈርሰን ቡድን፡ እሷ ምን አደረገች? መጀመርያ፡ ዋንነስ ነበረች መሰለኝ፡ ከዛ ወጥታ አሴምብሊስ ተቀላቀለች፡ ከዚያ ወጥታ እራሷን በሌላ መንገድ አደራጀች፡ በቅርብ ጊዜ፡ በጥቂት ቡድን፡ ትንሽ ነገር ውስጥ ገባች።

262 በ ኦ ኤል ጃገርስ ስብሰባ ላይ ተቀምጬ ነበር። ሁላችንም፡ ኦ ኤል ጃገርስን እናውቀዋለን። አባቱ—የአሴምብሊስ ጀነራል ካውንስል እንዲመሰረት የረዳ ሰው ነው። አሁን፡ ኦ ኤል ታላቅ ሰው ነው። ታላቅ ሰባኪ ነው። ቅርብ ጊዜ፡ እንዲህ፡ አልኩት፡ “ወንድም ጃገርስ፡ እንዳንተ መስበክ ብችል ኖሮ፡ የፈውስ አገልግሎት እንኳ አይኖረኝም ነበር።” ያኔ በጀመረ ጊዜ ግን፡ ደም እና ወይን፡ የሚላቸው ነገሮች ነበሩት።

263 ወንድሞቼ፡ እዚህ ላይ፡ ስሜታችሁን ከጎዳሁት፡ ይቅር በሉኝ። እ—እ... መልካም። እግዚአብሔር ደም፣ ዘይት እና ወይን ማፍለቅ ይችላል፡ የፈለገውን ያድርግ፡ ይህ ግን ኃጢአትን አያስተሰርይም። ኖ፡ ሰር። ኖ፡ ሰር። ኖ፡ በጭራሽ። “የተዋጀች የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ኃጢአትን ማድረግ እስክትተው ድረስ፡ እስክትድን ድረስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃይሉን አያጣም።”

264 ደወልኩለና፡ ይዤው ሄድኩ፡ “ወንድም ጃገርስ? ” አልኩት። ያኔ ከክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ጋር ነበርኩ። እንዲህ አልኩት፡ “ወንድም ኑ ኤል? ” አልኩት፡

265 “የት ነህ ያለኸው ባክህ፡” አለኝ? አንድ ያረጀች እንግዳ ማረፊያ ቤት ውስጥ ነበርኩና። “እንዴ እዚያ ቤት ወሰዱኝ እያልከኝ ነው’ዴ? ” አለኝ፤

266 እንዲህ አልኩት፡ “አይ ፍላጎቴ ነው። እኔ ወዳንተ ሰመጣ፡” አልኩት፡ “ምን ነበር ያደረግከው? ስታትለር ሆቴል ውስጥ አስቀመጥከኝ፡ ጥግ ላይ ፈዝዤ ቆምኩኝ። ጠረጴዛው ላይ አስቀመጡኝ፡ የትኛውን ቢላዋ መጠቀም እንዳለብኝ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። እኔ አላውቅም… ኮቴን ሳልደርብ፡ ወርጄ፡ ያለኝን ሁሉ ባዶ ሊያስቀሩኝ ፈለጉ።” “ምን ማድረግ እንደነበረብኝ—አላወቅኩም፡” አልኩት።

“እነሱ ይህን ማድረግ አቅም ካጠራቸው፡ እኔ ወደዚያው ልውሰድህ፡” አለኝ።

267 “አይሆንም፡ ጌታዬ፡” አልኩት። “አሁን የፈለግኩህ፡ አንተው ከከፈልከው አብሬህ ስቴክ መብላት ፈልጌአለሁ፡” አልኩት።

“እሺ፡” አለኝ።

268 ከዚያም ወደ አንድ ቦታ ወጣንና፡ ተቀመጥን። “ወንድም ጃገርስ፡ እኔ ያንተ ነገር በእርግጠኝነት አደንቃለሁ… ” አልኩት፡

269 በጣም የምወደው፡ ድንቅ ወንድም ነው፡ ጓደኛዬ ነው። ያቺ… ከጉዞ ተመልሳ ወደዚህ የመጣች እጇ ላይ ደም እና ሌላ—ሌላ ነገር የነበራት ሴት ያለችበት፡ ትንሿ፡ የሱ በራሪ ወረቀት ይዣት ነበር። ስለዚህ አሁንም ይዣት ነበርና። ይህ ነገር ስሕተት ነው ብለህ ብትታመን ብዬዋለሁ፡ እና፡ በገዛ ራሱ ጋዜጣ ላይ—ይዤው ነበር።

270 “ልታደርገው የተዘጋጀህበት ነገር፡ እንዳለ ተረድቻለሁ፡ ለማድረግ የተዘጋጀህበት ትልቅ ሪቫይቫል አለ፡” አልኩት። ምክንያቱ፡ በርግጥም፡ እኔን ወደዛ የወሰዱኝ ቢዝነስ ሜን ናቸው።

271 ሰዎች የተረዱት ይመስለኛል። መንፈስ ቅዱስ በመድረክ ላይ መግለጥ ከቻለ፡ በየቦታው የሚካሄደውን ነገር ሊነግረኝ አይቻለውምን፡ ወንድሞቼ?

272 ቃል በቃል፡ ልነግራችሁ እችላለሁ፡ በወንድም ካርልሰን እና **በዚህ** ወንድም ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። ትናንት በሰብሰባ ላይ ተቀምጠን ነበር፡ እና ዛሬ ጠዋት በዚህ ቦታ ምን እንደሚሆን፡ ለእነዚህ ወንድሞች ነግሬአቸዋለሁ። ይህ እውነት ነው። በትክክል። አያችሁ? ምክንያቱ፡ መንፈስ ቅዱስ ቀሰቀሰኝና “መሰኮቱ አጠገብ ቁም፡” አለኝ። በመሰኮት፡ አየሁ፡ እና በትክክል **ይህንን** አሳየኝ። እንዲህ አልኳቸው፡ “ወንድሞች ሆይ፡ አሁን… ” [አንድ ሰው፡ “እውነት ነው” ብሎ ተናገረ።—አርታዒ።] ይህን በዚያ! በትክክል አሳይቻችኋለሁ። አያችሁ?

ለምን፡ ሊያውቁት ስለሚገባቸው ነው።

273 ቅርብ ጊዜ፡ እዚህ በቻታውኳ፡ አንድ ሰው ተነሳና፡ “ወንድም ብራንሃም ነብይ ነው፡” ብሎ ተናገረ። እኔ ሰለ ራሴ ነብይ ነኝ አልልም። አያችሁ? እርሱ ግን፡ “ወንድም ብራንሃም በመለየት ጸጋ መንፈስ ስር ሲሆን ነብይ ነው፡ ነገር

ግን፡” “ኦህ፡ ዶክትሪኑ መርዝ ነው። ራሳችሁን ጠብቁ፡” አላቸው። የተማረ ሰው፡ እንዴት እንዲህ ይናገራል፡ ብዬ አሰብኩ?

274 **ነብይ** ማለት ምን ማለት ነው? “የቃሉ መለኮታዊ ተርጓሚ ማለት ነው።” “የጌታ ቃል ወደ ነቢዩው መጣ፡” እያችሁ። ያ ግን፡ መሰማትም መናገርም፡ አይደለም።

275 ለማንኛውም፡ ግን፡ ወንድም ጃገርሰ። ተናገርኩትና፡ ኦህ... አለኝ፡ “በእጇ ደም ስለነበረባት ሴት ስለሷ እይቺዋለሁ፡” አልኩት።

276 “ኦህ፡” “ወንድም ብራንሃም፡ እስካሁን ካየኳቸው ክሰተቶች እጅግ የሚገርም ነገር እሱ ነው!” አለኝ።

277 “ወንድም ጃገርስ፡ እወድሃለሁ። በመጀመሪያ፡ እጄን በእጅህ ላይ አድርገውና፡ ወንድማማቾች ነን እንባባል፡” አልኩት።

“አዋን። ምንድነው ችግሩ? ” አለኝ፡

278 እንዲህ አልኩት፡ “ከማውቃቸው ታላላቅ ሰባኪዎች አንዱ ነህ። ለእግዚአብሔር እንዴት ያለ—ግሩም መሣሪያ ነህ!”

279 “አመሰግናለሁ ወንድም ብራንሃም፡ አንተ በእውነት ትሑት ሰው ነህ።” አለኝ።

280 “ይህን ያልኩህ፡ ትሁት ለመሆን አይደለም። ይህን ያልኩት እንዲህ እንደሆነ ስለማምን ነው። አንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነህ።” እኔ ግን እልሃለሁ፡ “ወንድም ጃገርሰ፡ እንዲህ ካላደረግህ በቀር... እጅግ አብዝተህ—መሰመር እየሳትክ ነው፡ ስለምትናገረው ነገር ምላሽ መሰጠት የምትችልበት ሚዛን አይኖርህም። መሰረትህ... ”

281 እና የብዙዎቻችሁ የአሴምብሊሰ ኦፍ ጋድ፡ እና ሌሎች ሰዎች፡ በእነዚህ የፈውሰ አገልግሎቶች ላይ ያላችሁ ጉዳይ ይህ ነው። እኔ እናንተን አልወቅሰም። ብዙ የሚባል ነገር አለ... እዚጋ፡ ቶሚም፡ እጅግ የሚደንቅ ወንድም ነው። ዛሬ ግን በመለኮታዊ ፈውሰ ሰም በምድሪቱ ላይ ብዙ ነገር አለ፡ በከተማ ውስጥ ሰብሰባውን ስፖንሰር ማድረግ አለመፈለጋችሁ ምንም አያስገርምም። መጥተው ህዝቡን ያደማሉ፡ ይወጣሉ። እና ምን አገኙ? እናንተ ከመድረክ፡ ከፑልቢታችሁ ከምትሰጧቸው የተሻለ፡ ለህዝቡ አንዳች አይጨምሩላቸውም። እና ወንድሞች ሆይ፡ ትክክል ናችሁ። እኔ እላችኋለሁ፡ ልክ ናችሁ። ግን ልክ እንደ...

282 የማርቲን ሉተርን ታሪክ እያነበብኩ ነበር። “ማርቲን ሉተር የካቶሊክን ቤተክርሰቲያንን መቃወም መቻሉ፡ እንቆቅልሽ አልነበረም፡” ይባላል። የእሱን ታሪክ አንብባችኋል። “ማርቲን ሉተር የእሱን መነቃቃት ተከትሎ በመጣ ወግ አጥባቂያን ሁሉ በላይ ጭንቅላቱን መያዝ መቻሉ ግን፡ ሚሰጥር ይህ ነበር።”

283 ክሰተቱ ካለፈ በኋላ፡ በግብጽ እንደነበረ፡ ያልተገረዙት ተከተሉ። ይህም ደግሞ በምድሪቱ ላይ ሁሉጊዜ ችግር ይፈጥራል። እዚያ ላይ ሰንደርሰ፡ እናውቀዋለን። ይህም፡ ቆሬን አሰነሳው፡ እግዚአብሔርም እሱን አጠፋው። ነገር ግን፡ ወንድሞች ሆይ፡ እኔ እናንተን አልወቅሰም።

284 ወንድም ጃገርሰ ቁጭ ብሎ ያንን ያደረገው መንፈሰ ቅዱሰ መሆኑን ሊነግረኝ ሞከረ። ተናገረ... እኔ በገዛ ጋዜጣው፡ የያዝኩት ነገር ነበረ... እኔም

አልኩት፦ “ወንድም ጃገርስ፡ አሁን፡” እኔ አልኩት፡ “የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። አንተ የነገር መለኮት ዶክተር ነህ፡ የተማረ ጠበቃ ነህ። እድገትህ እጅግ ንጹህ በሚባል፡ በተረጋጋ ቤተ ክርስትያን፡ በአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ነው። አባትህም ያንን እምነት እንዲቆረቆር የረዳቸው ሰው ነው። አንተ ግን ከዚህ አፈነግጣለሁ ካልክ፡ አንተን የሚመለከት ነው።” እንደ’ኔ አልኩት፡ “ይህን አደርጋለሁ ለሚል ሰው፡ ለሰውዬው ይመለከታል። እኔ ምንም አይነት ድንበር አላደርግም። ነገር ግን እንዳንተ ያለ አገልጋይ፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሳትን ለክርስቶስ ማምጣት ሚችልበት ሰው ግን፡ አገልግሎትህ በስሜት መሰረት ይገነባልን።” እንዲህ አልኩት፦ ወንድም ጃገርስ፡ **እንዲህ** አይነት ምሰሶ ሰትገነባ፡ ለዚያ የሚመጥን የመልስ ሚዛን ከሌለህ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይወድቃል። ስለምትናገረው ነገር ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሊኖርህ ያስፈልጋል።”

“መጽሐፍ ቅዱስ ቃል አለኝ፡” አለ።

“እስኪ አውጣው፡” አልኩት።

285 አለኝም፡ “ደህና፡ ወንድም ብራንሃም፡” “ያንን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው፡” አለኝ።

286 እኔም እንዲህ አልኩት፡ “መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አርጎ፡ ከሰዎች ዘንድ ደም ያወጣበት፡ እና ሌላ ሌላ ነገር ያደረገበት፡ ቃል አሳየኝ። ከውስጣቸው ዘይት የቀዳበት፡ ቃል አሳየኝ። ‘ዘይቱ ስለ መለኮታዊ ፈውስ ነው፡’ ብለሃል። ‘የዚያች ሴት ደም ደግሞ ለዓለም ህዝብ ሁሉ መዳኛ ይሆናል፡’” ብለሃል። አልኩትም፡ “እንዲህ ከሆነ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምን ይሰራል? ተጻራሪ ነው። የሚቃወመው ሁሉ፡ ጸር ነው። የሚቃወመው ነውና።” “ጸረ ክርስቶስ ዶክትሪን ይሆናል፡” አልኩት።

“ኦህ፡” “ወንድም ብራንሃም፡ አንድ ቀን ትማራለህ፡” አለኝ።

287 “ወንድሜ፡ እንዲህ አይነቱ ትምህርት፡ እንደልማር ተስፋ አደርጋለሁ፡” አልኩት። “አንተ ወንድሜ ነህ፡ እወድሃለሁ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፦ “ወንድም ጃገርስ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ የማትወጣበት አዘቅት ውስጥ፡ ትገባለህ። ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ተመለስ ወደ ወንጌል ተመለስ።” “በስሜት መሰረት ላይ አትገንባው፡” አልኩት። “ይህም... ” አልኩት፡

288 እንደምታውቁት፡ አሁን፡ ለዘለአለም ህይወት እያጠመቃቸው ነው፡ “በተጠመቃችሁ ቁጥር፡ ወጣት ሴት እና ወንድ ትሆናላችሁ። ወደፊት... (በፍጹም) አትሞቱም።” እነዚያን “የሙት ባሕር ቫይታሚን ክኒኖች፡” ስለዚህ፡ ያ፡ አሁን፡ በአዘቅቱ መጨረሻ ላይ ደርሷል። አየህ? ግን ያ ነው፡ ወንድሜ፡ በእነዚያ ትንሽ ስሜቶች ትጀምራላችሁ።

289 እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ያላችሁ ሰዎችም፡ እንደዚህ ያለ ነገር ወደ ከተማይቱ ስታስገቡ፡ ዲያብሎስም፡ ብልጥ፡ እንደሆነ ታውቃላችሁ እንደዚህ ባሉ ነገሮች ላይ—ዘሎ ይገባበታል። ወሬ ያናፍስበታል። ሰዎች—እንዲጎዱ ያደርጋል፡ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ግራ መጋባት ይዘራል፡ ወዘተረፈ። ነገሩ ግን እንደዚያ አይደለም።

290 አሁን፡ እዚህጋ። የቱንም ያህል ትክክል ብትሆኑም፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ የምንስናከልበት እና የምንሰትበት አንድ ነገር ይህ ነው። አሁን ይህን ተናግሬ፡

እዘጋለሁ። የቱንም ያህል ትክክል ብሆን፡ የቱንም ያህል መጽሐፍ ቅዱስ ቢደግፈኝ፡ የቱንም ያህል የእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ይኑረኝ፤ በልቤ ውስጥ ግን፡ ለሰው ዘር እና ለሁሉ የሚሆን የእግዚአብሄር፡ የፍቅር መንፈስ፡ ከሌለኝ፡ ገና ከጅምሩ ሰቻለሁ።

291 አሁን፡ ጳውሎስ፡ በአንደኛ ቆሮንቶስ 13 ላይ፡ “እውቀት ቢኖረኝም፡ አለ፡ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሁሉ ባውቅ፡ አለ፡ ሁሉንም፡ ባውቅ፡ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፡” እነዚህ ለእግዚአብሄር ብቻ የምትናገሯቸው፡ ሁል ጊዜም የማይተረጎሙ ናቸው። “በልሳኖች ብናገር፡ በሰዎችና በመላእክት ትክክለኛ ልሳን ብናገር፡ ፍቅር፡ ፍቅር ከሌለኝ፡ ምንም አይጠቅመኝም።” ስለዚህ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሁሉ አውቄ፣ እና ፈታትቼ እና—እና ሁሉንም አንድ ላይ እንዲሰምሩ ማድረግ ብችል፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ፡ ምን ይጠቅማል? መቼም...

292 ኢየሱስም አለ፦ “ይህ ሲኖራችሁ፡ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ... ” አሴምብሊሶች ዋንነሶችን ሲወዱ፡ ዋንነሶችም ለአሴምብሊሶች ፍቅር ሲኖራቸው፡ ትክክል ሁኑ አትሁኑ፡ “እርስ በርሳችሁ፡ ስትዋደዱ።” ግባችሁ የተሳሳተ እስከሆነ ድረስ፡ የልብ አሳባችሁም ብልሹ ነው፡ ማለት ነው፡ ስለዚህ ገና ከጅምሩ ሰታችኋል። እውነት አይደለምን? አያችሁ፡ “በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ፡ ከንቱ ነኝ።” እግዚአብሔር፡ ፍቅር ነውና። ያንን እናውቃለን።

293 እኔ በልሳኖች በመናገር አምናለሁ። ለምሳሌ አንድ ሰው፦ “ወንድም ብራንሃም በመጀመርያ ማስረጃ አያምንም፡” ሊል ይችላል። ያንን አሁን ከእናንተ ጋር ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። አያችሁ? ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።

294 አንድ ሰው ክርስቶስን ሲቀበል፡ የመንፈስ ቅዱስን ቀብድ እንደሚቀበል አምናለሁ። ምክንያቱም፡ ኢየሱስ ሲናገር፡ በማቴዎስ—ምዕራፍ 12 ላይ፡ 5ኛ ምዕራፍ ከቁጥር ሃያ-... 24ኛው ቁጥር፡ እንዲህ አለ። አይደለም፡ ቅዱስ ዮሐንስ 5:24 ይመስለኛል። እንዲህ አለ፡ “ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።” እንግዲህ፡ አንድ የዘለአለም ህይወት አለች። “ከሞት ወደ ህይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ኩነኔ አይመጣም።”

295 ማንም ሰው ራሱን መጥራት እንደማይችል አምናለሁ፡ እግዚአብሔር ሊጠራው ይገባልና። እግዚአብሔር ከጠራው... ወንድሞች ሆይ፡ እንደምናውቀውም፡ እግዚአብሔር እንደጠራቸው የሚያስመስሉ፡ ብዙ ሰዎች እናዳሉ እናውቃለን፡ ሕይወታቸው ግን በቅርቡ... ይገለጣል፡ ታውቁታላችሁ። እግዚአብሔር የጠራህ ከሆንክ ግን፡ እንዴ፡ የትም አትሄድም፡ ትጸናለህ፡ ጸንተህ ትጠብቃለህ፡ አየህ፡ ታውቃለህና። እንዲህ ከሆነ ግን... እናንተም፡ ታውቁታላችሁ። ይሄ፡ የባፕቲስት ዶክትሪን አይደለም።

296 እጅ ለእጅ በመጨባበጥ ዘለአለማዊ ደህነንት ይገኛል ብዬ፡ ወዘተረፈ እኔ አላምንም። እኔ—በዛ አላምንም፡ በጭራሽ። እነሱ ያንን ማመን ከፈለጉ፡ ችግር የለውም፡ ይሁንላቸው። አሁንም ወንድሞቼ ናቸው እላለሁ።

297 ዛሬ ጠዋት፡ አንድ ቁራሽ ፓይ ካማረኝ፡ (የእራት ጊዜ ሊቃረብ ነውና)፡ እኔ ቼሪ ሊያምረኝ ይችላል፡ እናንተ ግን አፕል ልትወዱ ትችላላችሁ፡ ሁለታችንም

የምንበላው ግን ፓይ ነው። አያችሁ? ስለዚህ ፓይ እስከበላን ድረስ... ምን ልዩነት ይፈጥራል።

298 እኛ የምናምንበት መንገድ ይህ ነው። ዋንነስ መሆን ከፈለጋችሁ ዋንነስ ሁኑ፡ አሴምብሊ ኦፍ ጋድ መሆን ከፈለጋችሁ፡ አሴምብሊ ኦፍ ጋድ ሁኑ። ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ መሆን ከፈለጋችሁ፡ በውስጡ ክርስቲያን ሁኑ። አያችሁ?

299 ለራሳችሁ—ፈልጉ፡ ነገር ግን በዚህ ምክንያት አትጨቃጨቁ። ምክንያቱ፡ እነዚህ ትንንሽ ነገሮች፣ ሁሉም በአንድ ላይ ይተሳሰራሉ። ትክክል ነው። ሁሉም በአንድነት ተሳስረው ወደ አንድ ቦታ ይመጣሉ።

300 እና—ደግሞ ምንም ነገር ብንሰራም፡ ብዙ ተአምራቶች ብናደርግም፡ ምንም ያህል ተራሮች ማፍለስ ብንችልም፡ ምንም ይሁን፡ ወደምንወደው ስፍራ እስክንደርስ ድረስ፡ አስመሳይ-እምነት ሳይሆን፡ ነገር ግን እርስ በርስ እንዋደድ። ወንድሞችን ሁሉ ስንወድ፡ ከየትኛው ቤተ ክርስትያን ይሁን፡ እንውደዳቸው፡ ምክንያቱ፡ የሐይማኖት ሐሳብ እንደሆነ እናውቃለንና፡ እንደምንወደው ማስመሰል ሳይሆን፡ "መውደድ ይጠበቅብናል።" ይሄን ማድረግ ከቻልን፡ ግን፡ እርስ በርስ እንዋደዳለን፡ ከዛ በኋላ፡ ትዕግስት፡ እርስ በርሳችን መሸካከም ይኖራል።

301 ይመስለኛል፡ በቆላስይስ 3፡ ወደ 9፡ አካባ... እ—እ እንጃ፡ ብቻ፡ ይመስለኛል... ቃሉን አሳስቼ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን እንዲህ ይላል። ክርስትያን ከሆንን በኋላ ምቀኞች እንሁን። አያችሁ? አንዳችን ለሌላው በመከባበር እና በመሞጋገስ እስከሞከርን ድረስ እምነት ሊኖረን አይችልም። አያችሁ፡ አይሆንልንም፡ እምነት አይኖረንም። አያችሁ፡ እግዚአብሄርንን ማክበር፡ እሱን ማክበር ይሻለናል። እውነት ነው፡ ወንድሞቻችንን እናምናቸዋለን፡ ይህም ፍቅር ነው፡ ክብር እና ሙገሳው ግን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው! በዚህ ጉዳይ ግን... አንዳችን በአንዳችን ላይ መተማመን እና ድፍረት ይኑረን። "እንወሻሽ።" ገብቷችኋል? "አትወሻሹ።" ዛሬ ጠዋት "እውዳችኋለሁ፡" ካልኳችሁ፡ ከልቤ ማለት አለብኝ። ካልሆነ ግን፡ ግብዝ ነኝ። ትክክል።

302 አሁን ወንድሞች በዚህ ጉዳይ ላይ... ወንድም ቶሚ፡ ብዙ እንዳልያዝኩብህ፡ ተሰፋ አደርጋለሁ። እ... ወንድም ቶሚ በአንድ ሰከንድ ውስጥ የሚናገረው ነገር ይኖረዋል። ነገር ግን በመካከላችሁ ሳለሁ ይህን ልበል...

303 ይህን አምናለሁ። እግዚአብሄር አባታችን ማርያም በተባለች ድንግል ላይ ጥላውን እንዳጠለለባት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለውን የእግዚአብሄር ልጅ ይወለድ ዘንድ፡ በሷ ዘንድ የደም ህዋስ እንደፈጠረ፣ በእርሱም ዘንድ እግዚአብሔር ራሱ፡ በስጋ፡ ተገልጦ በመካከላችን ማደሩን አምናለሁ። "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ፡ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና።" ያ የደም ሕዋስ ለኃጢአታችን ስርየት፡ በቀራንዮ እንደፈሰስ አምናለሁ። መንፈሱም ከእርሱ ወጥቶ ሄደ ወደ ቤተክርስቲያኑም ተመልሶ መጣ፡ 'ምክንያቱም፡ ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ሎጎስ የሆነው፡ ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በጥምቀት፡ በእኛ ዘንድ ሆኗልና። ይህም... ክርስቶስ እራሱን ቆርሶ፡ ህይወቱን

ለእያንዳንዳችን ማካፈሉ ነው፡ ይህም፡ እንደ ሰዎች፡ በአንድነት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን እንሆን ዘንድ ነው። እና በቅርብ ጊዜ...

304 ታውቃላችሁ። ድሮ እጋልብ ነበር። አባቴ ፈረሰኛ ነበርና፡ በጣም ጥሩ ገሪ ነው። እኔም እጋልብ ነበር። በአራፓሆ ሜዳ ውስጥ፡ ማለቴ—ከአራፓሆ ክልል በላይ ያለውን ትረብልሳም ወንዝ አጠገብ... ነው እናሰማራቸው ነበር። የሄሬፎርድ ማህበር ያንን ሜዳ ያሰማራበት ነበር። አርቢዎች ሁሉ፡ በዚያ ሜዳ አጠገብ—የሚያሳድጉት፡ በጣም ብዙ ሣር ነበረ። እና እርባታው አንድ ቶን ሳር ማምረት ከተቻለ፡ ከብቶቹን—ግጦሹ ላይ ማስገባት ትችላላችሁ፡ ቦታው ከእስቴስ ፓርክ በታች ነውና፡ ከብቶቹን በዚያ ማሰማራት ይቻል ነበር-... የእኔ ታላቅ የአደን ግዛቴ፡ በዚያ ነበረ። ለአንድ አመት ሙሉ እዚያ ውስጥ አርብቻለሁ። ሄጄ፡ በፀደይ እና በውርጭ ጊዜ፡ ሰወጣ እና ሰችል፡ እዚያ ላይ ለመሆን ብቻ፡ ዙሩን እጋልባለሁ፡ መጋለብ ስለምወድ ነው። በሜዳው ሁሉ ዙርያ-... ከላይ-እስከ-ታች ድረስ፡ እዚህ የመግባት እና ከብቶቻቸውን የማሰማራት መብት ያላቸው፡ ብዙ አርቢዎች አሉ። እና በጸደይ ወቅት፡ ብዙ ጊዜ፡ ከብቶቹን አንድ ላይ እንዲያሰባስቡ እና እዚያ እንዲሮጡ እረዳቸው ነበር።

305 እና በዚያም የከብቶች ማገቻ አጥር ነበረ፡ ይህም ከግጦሽ ሲመጡ፡ እንዳይመለሱ ወደ ሌላ ሰው ንብረት እንዳይገቡ። እስከ... አጋቹ ቆሞ ከብቶቹን ወደ ውስጥ ሲገቡ፡ ይቆጥራቸዋል። እኔም ብዙ ቀናት፣ ከሰዓት ወደ ሰዓት፣ ብዙ ሲያልፉ፡ አቶ ግሪምስን እየዋለሁ፡ ዳይመንድ ባር ነበረውና፡ የኛ ተርኪ ትራክ ነበረች፡ ከእኛ በታች የነሩት—እነ ትሪፖድም፣ እነ ጀፈሪስ ወዘተ። ከዛ ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት፡ እግሬን በኮርቻው ቀንድ ላይ ሳደርግ፣ እረኛው በዚያ ቆሞ፡ ከብቶቹን ሲቆጥር ቁጭ ብዬ እታዘበዋለሁ።

306 እና አንድ ነገር አስተዋልኩ። የተለጠፈባቸው ብራንድ ብዙ አያስጨንቀውም። ነገር ግን በትክክል የሚፈልገው አንድ ነገር ነበረው፡ ይህም የደም መለያቸውን ነበር። መለያው ሰሩበርድ ሄርፎርድ ካልሆነ በቀር አጥሯን የሚያልፍ አይኖርም፡ ብራንዱ ልዩነት አይፈጥርበትም ነበር።

307 አሁንም እንደሚመስለኝ በፍርድ ጊዜ እንደዚያው ይሆናል ብዬ አስባለሁ። የእኛን የደም መለያችን እንጂ፡ የብራንድ ስማችን አያይም።

308 ወንድሞቼ፡ ስህተቶቼን ሰርቻለሁ፡ እና ብዙ ስህተት የሆኑ ነገሮችን ሰርቻለሁ። አሁንም በቆይታዬ ላይ አሁን ከተናገርኩት፡ ወይም ካልኩት ነገር በሆነ መልኩ የሚያመሳጭ ሆኖ ከተሰማችሁ፡ ወይም ዛሬ ጠዋት ቁጣ የሚያነሣሣ ነገር፡ ሰናገር ከሰማችሁኝ፡ እንደ ክርስቲያን ወንድም ወይም እህት፡ ይቅር እንድትሉኝ እጠይቃችኋለሁ። ቁጣ ለመቀስቀስ አስቤ አይደለም። እውቀት ይኖረን ዘንድ፡ ልቤን በፊታችሁ አፈሰስኩ።

309 የሚጠመቅ ሰው ካለ፣ እናንተ ወንድሞች፣ ራሳችሁ አድርጉት፡ እሺ። ይህ፡ እኔ—አላደርገውም። ማጥመቅ ካለብኝ፡ የማጠምቀው፡ እንደነገርኳችሁ እንደዚያው ነው። ከመካከላችሁ አንዳችሁ ማድረግ ትችላላችሁ፡ እያችሁ። ስለዚህ ሰውየውን መውሰድ ትችላላችሁ፣ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃሉ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰምም፡ የተጠመቁ አሉ። አንዱን አጥምቄ ቢሆን... በርግጥ እስከ አሁን አላጠመቅኩም። የማጠምቀው በራሴ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፡ በዚያ ያሉትን ሰዎች ብቻ። በቤተ ክርስቲያኔ ያሉ

ሰዎች የሚጠመቁት በዚያ መንገድ ነው። ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ካያችሁ፡ የቆየ ሚሲዮናዊ ስርዓት ነው፡ የቆየው መጥምቃዊ የባፕቲስት ስርዓት ነው። እንግዲህ… ይህም ቢሆን።

310 በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምናለሁ። በመንፈስ ቅዱስ በ—በልሳኖች በመናገር አምናለሁ። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ በሰጣት ስጦታ ሁሉ አምናለሁ። አንድ መቶ ፐርሰንት እኔም አለሁበት። ነገር ግን…

311 ዛሬ በዙሪያችን ባሉት ጥራዝ-ነጠቅ ፈውሶች ግን የለሁበትም። እዚህ ላይ አንድ አስተያየት መስጠት እፈልጋለሁ። ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ወንድም ነበር… እንደ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ የምቆጥረው፡ ውድ ወንድሜ ቶሚ ሂክስን አልነበረም። በሌላ አገር ውስጥ ሌላ ሰው ነበርና፡ በዚያ አገር ውስጥ… እንደምታውቁት፡ ሁል ጊዜ፡ “የእግዚአብሄር ጥራዝ-ነጠቅ ፈዋሽ! ጥራዝ-ነጠቅ ፈዋሽ፡” ዓይነት፡ ሰው ነው።

312 እናም ሰውዬው ከጨረሰ በኋላ… ከሉተራን ቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ ደረሰኝ። ፀሀፊዬ በመዝገብ ይዘን እንዳስቀመጥነው ያውቃል። የሰውየውን ስም አልጠራም፡ ክርስቲያናዊ-አይደለምና። ምንም እንኳን፡ በዚያ ሰውዬ አሳብ ባልስማማም፡ ችግር የለውም። እወደዋለሁ። ወንድሜ ነው።

313 ብቻ ግን አንዳንድ በሚያደርጋቸው ስሜታዊ ነገሮች ተወሰደዋል፡ ስተዋል፡ ወይም እንደዚህ ባለ ነገር ተወሰደዋል፡ እሺ። እና፡ ያ ነገር፡ ጥሩ አይደለም፡ እሺ። ወንድሜ… “የሰውነት እንቅስቃሴ ጥቅሙ ትንሽ ነው።”

314 እና ይህ የሉተራን አገልጋይ አ—አ— ለአገልጋዩ አንድ ደብዳቤው መልሶ ጻፈለት። እንዲህ አለ፡ “እናንተ ወደዚህ የምትመጡ የአሜሪካ ወንጌላውያን፡” አለው፡ “ሰውን ሁሉ ከሚፈውሰው ጥራዝ-ነጠቅ ፈውሳችሁ!”

315 እንግዲህ ይህ ለኔ ቆንጆ የአበባ እቅፍ ይመስላል፡ እንደዚያ ማለቴ እንዳልሆነ ግን እግዚአብሔር ያውቃል። “ግን፡” እሱ እንዲህ አለ፦ “ያኔ— ትንሿ ህጻን ዲቦራ ስታድስክሌብ፡ በሞተች ጊዜ፡ ያቺ እናት በዚያ ቀን፡ በህ-… ህጻኗ በሞተችበት ጊዜ፡ በካሊፎርኒያ ፈጽማ ቀዝቅዛ ነበር። ህጻኗ በወንድም ብራንሃም እቅፍ… አይቻታለሁ፡ እኔ አጠገቡ ቆሜ ለህጻኗ ጸለየላት። ህጻኗም ወድያው ማልቀስ እና መራገጥ ጀመረች እና፡ ለእናንቷ መለሰላት።”

316 የሜክሲኮን ጉዳይም ያውቀዋል። ይህንን የፋል ጎስፔል ቢዝነስ ሜን ንግግር ዋቢ ማድረግ እንችላለንና። ከዶክተር የተጻፈ ምስክር ሊኖርህ ይገባል። ያ የሜክሲኮ ሕፃን፡ ጧት በዘጠኝ ሰአት ሲሞት፡ እና ያን ቀን ማታ አስራ አንድ ሰዓት ነበርና። ዶክተሩ የምስክር ወረቀት ጽፏል። ብዙዎቻችሁ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ወንድሞች የምታውቁት ወንድም እስፒኖዛ፡ ከዶክተሩ እጅ፡ የሞት ምስክር ወረቀት የተቀበለው እሱ ነው።

317 እና ሜክሲኮ ሲቲ ውስጥ ሃያ ሺህ ካቶሊኮች ወደ ክርስቶስ በመጡ ቀን፡ በህዝቡ መካከል ራእይ አየሁ። “ህጻኑን፡ አላውቀውም… እዚሁ ግን ራእይ አይቻለሁ። ዝም ብላችሁ አትውሰዱት፡” አልኳቸው።

318 እና ቢሊ፡ ከሰላሳ ወይም ከአርባ አስተናጋጆች ጋር፡ አብሮ፡ ያቺን ምስኪን ሴት ከያዘችው ህጻን ጋር፡ ከፀሎት መስመር ማሰወጣት አልቻለም።

ከእግሮቻቸው ስር፡ በዛ በዚህ ትሮጣለች። ከዛ፡ በመጨረሻ፡ ጃክ ሞርን ላክሁባቸው። “ሂድና፡ ጸልይላት፡” አልኩት።

319 ወደዚህ ተመለከትኩና፡ ትንሽ የሜክሲኮ ሕፃን ፈገግ ሲል አየሁ። “እንዴ ቆዩ። ወዲህ አምጡት፡” አልኳቸው። አያችሁ? እና እጆቼን በዚያ በብርድ ልብስ ላይ ሳደርግ... ቀኑን ሙሉ፡ ዝናብ ሲዘንብ ውሏል። ከጠዋት ጀምረው ቆመው ውለዋል፡ አሁን ከምሽቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበር። እና እጆቼን በሕፃኑ ልጅ ላይ ጫንኩበት። ወድያው መራገጥ እና መጮህ ጀመረ። ሁሉም መጯጯህ ጀመሩ።

320 እና፡ ልጁን ከተሰጠው ምስክር ወረቀት ጋር ሄዱ። ወደ ዶክተሩ ሄዱ፡ ዶክተሩም አላቸው፦ “ህጻኑ ዛሬ ጠዋት በዘጠኝ ሰዓት፡ እንደሞተ ተናግሬአለሁ። የሞተው በኒሞንያ ነው።” አያችሁ? እነዚህ ነገሮች በሙሉ—እውነት—ናቸው። ቃል ናቸውና። መሆንም አለባቸው።

321 ስለማንኛውም ነገር ሁል ጊዜ ሐቀኛ እና እውነተኛ መሆን አለብን። ሌላ ነገር አታስመስሉት... እንደሆነው እንዲሁ ይሁን። ይሁን... አያችሁ፡ አ—አ—አምላክ ነውና። እግዚአብሔር የማንም እርዳታ አይፈልግም።

322 ስለዚህ እንዲህ አላቸው፡ “ያቺ እናት አሜሪካ ወደሚኖረው ወንድም ብራንሃምን ስትደውል፡ እያለቀሰች ‘ናና ልጄን ከሞት አንሣልኝ!’ ብላ በሰልክ ስትጠራው፡ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት... ”

323 ባልዋ በሰራዊቱ መካከል ቄስ ነውና። ጁሊየስን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ፡ ብዙዎቻችሁ ታውቁታላችሁ፡ **አፍሪካን የጎበኘ ነብይ** የሚለውን መጽሐፌን የፃፈ።

324 ያቺ ምስኪን የኖርዌያዊት እናት፡ ድምጿን ከፍ አድርጋ እያለቀሰች፡ እንዲህ አለች፦ “ወንድም ብራንሃም፡ ያ ሕፃን ወደ ሕይወት ሲዘራ፡ እኔ እዚያ ቆሜ ነበር!” “የክርስቶስ አገልጋይ መሆንህን... እናምንሃለን፡” አለች። “ናና፡ በልጄ ላይ እጅህን ጫንበት፡ በህይወት ይኖራል፡” አለች። ለአራት አምስት ሰዓታት ያህል ታመመ፡ ከአንድ ወይም ከሁለት፡ ከአፍታ በፊት፡ በኒሞንያ ህይወቱ አለፈ።

325 እና ብዙ ሰዎች በዙርያቸው ነበሩ፡ ላይ-ታች-ይዘላሉ፡ ይጮኻሉ፡ ያወራሉ፡ እንዲህ እያሉ “እግዚአብሔር ያስነሣዋል! እግዚአብሔር ያስነሣዋል!” እንዲህ ይናገራሉ...

326 በዚህም፡ የአሜሪካ አየር-... ወይም የአሜሪካ አየር መንገድ። የዩናይትድ ስቴትስ የጦር ጄት፡ በአንድ ቀን አድርሶ፡ ሊመልሰኝ ተዘጋጅቶ ነበር። አያችሁ?

327 እኔ ግን “ከመውጣቴ በፊት፡ የጌታን ፈቃድ ልለምን፡” አልኳቸው። ስለዚህ፡ ለሁለት ቀናት ጸለይኩ። ያ ዶክተር ህጻኑ እዚያ እንዲያርፍ ማድረጉ በጣም መልካም አደረገ።

328 ከዚያም፡ አንድ ቀን ጠዋት ተነስቼ ወደ ኩሽና እየሄድኩና። ዞር ብዬ ሳይ፡ ያንን የሚያክል ብርሃን፡ እዛጋ ቆሞ፡ ሲሽከረከር፡ አየሁት፡ እና፡ “አትንካው። አትገሰጸው። የእግዚአብሔር እጅ ነውና” አለኝ።

329 ወዲያው ሮጬ ወደ መንግስት ደወልኩና፡ “አይ—አይ መምጣት አልችልም፡” አልኳቸው።

330 እናም ይህ የሉተራን አገልጋይ እንዲህ አለ፡ “እንደ ወንድም ብራንሃም ከእግዚአብሔር ዘንድ አጭርና-ግልጽ ውሳኔ እስክትቀበሉ ድረስ ለምን አትታገሱም? ከዛ በኋላ ስለምትናገሩት ነገር ታውቃላችሁ።”

331 አሁንም፡ ይህ ነው፡ ወንድሞቼ፡ ዝም ብለን መደምደሚያ ላይ ሳንደርስ፡ ከእግዚአብሔር፡ አጭርና-ግልጽ ውሳኔ፡ ብንጠብቅ መልካም ነው።

332 የምናየው ነገር ሁሉ፡ ስለ እግዚአብሔር ምንም ያልተረዱ ሐጢአተኞችን መፈወስ። መለኮታዊ ፈውስ በመርህ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እምናለሁ፣ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር መምጣት አለባችሁ፡ ልባችሁን ለእርሱ ስጡ፡ ህይወቶቻችሁንም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እጠቡ፡ ከዚያም እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል ፈውሳችሁን መስራት ይጀምራል። እያችሁ፡ ልክ ይህ ወንድም፡ ስለዛች ቅድስት የእግዚአብሔር ሰው፡ እዛ ስለጸለየላት እንደተናገረው ነው።

333 በህይወቴ፡ ብዙ ስህተቶችን ሰርቻለሁ። ብዙ የተሳሳቱ ነገሮችን ሰርቻለሁ። እኔ ምናልባት፣ ረጅም ዕድሜ ከኖርኩ፣ ብዙ ተጨማሪ እሳሳታለሁ። ምናልባት አንዳንዶቹ በመንገድ ላይ እንቅፋት ሊሆኑባችሁ ይችላሉ። ይቅር እንድትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

334 ስለ አብራሃም፡ ስለ ነበሩበት ግራ መጋባቶች እያነበብኩ ነበር። እንዴት እሱ፡ አቤት፡ የሰራቸው ነገሮች ሁሉ፡ እንዴት እግዚአብሔርን እንደተጠራጠረው ስለሚስቱ እንዴት እንደዋሸ፡ ወዘተ። ነገር ግን ስለሱ መለኮታዊ ምስክርነት በሮሜ ምዕራፍ 4 በተጻፈ ጊዜ፡ ስህተቶቹን ፈጽሞ አልጠቀሰም፡ ነገር ግን፡ አብራሃም… በእግዚአብሔር ዘንድ “በረታ እንጂ” “በአለማመን ፈጽሞ አልተወላወለም።” የህይወቱ መለኮታዊ ምስክርነት በተጻፈ ጊዜ ግን፡ ስህተቶቹ ሁሉ አንድም ሳይቀር ተረሱ። ግራ መጋባቱ ሁሉ አልተጠቀሰም። ስሕተቱ ሁሉ አልተጠቀሰም።

335 ወንድሞች ሆይ፡ አንድ ቀን፡ የኔም የሕይወት ምስክር ሲነበብ፡ የኔንም፡ እንደሚጠራርግልኝ፡ መልሶም እንደማያሰባቸው ተስፋ አደርጋለሁ። እናንተም፡ እንዲሁ ታደርጋላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

336 [ዶክተር ቶሚ ሂክስ የሚከተለውን አስተያየት ሰጠ—እርታዒ።]

[ዛሬ ጠዋት የተነገረውን ሁሉ ለማጠቃለል እንደዚህ በማለት ማጠቃለል የምንችል ይመስለኛል፦ የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በእኔ ነው። እባካችሁ በሉት እስኪ። የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ነው።]

[በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ መውጣት-እና-መውረድ ሌሎች ነገሮችም አሉ። (አልናገርም።) መልእክት አለኝና። እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲሁ እንደነበረ እምናለሁ… ?… ኢየሱስ ሆይ… ?… ዛሬ ጠዋት ልቤ ተነክቷል፡ እና ለብዙዎቻችን አንዳንድ የሚረብሹን ነገሮች… ?… የበለጠ የእግዚአብሔር ሰዎች እና ሴቶች እንደሚያደርገን እምናለሁ።]

[ባቤ ሩት የሆሜሩን ንጉስ በመባል ይታወቅ ነበር። ነገር ግን ባቤ ሩትም የቀይ ካርድ ንጉስ እንደነበረ ታውቃላችሁ? ከተሳካለት ሆም ራን ይልቅ፡ ቀይ ካርዱ ይበዛልና። አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሠላሳ ጊዜ በቀይ ካርድ ወጥቷል፡ ሰምንት መቶ ሰላሣ ሆም ራንስ ብቻ አሸንፏል። ባቤ ሩት በቀይ ካርድ በወጣ

ቁጥር፡ ዳኛው “ወጥተሃል፡” ብሎ ይነፋለታል ወደ ቡድን መቀመጫ ይወጣል፡ ወደ ቡድን ማቆያ ይሄዳል፡ እጁን ያሻሻል ዱላውን ያነሣና አጥሩ ላይ እየጠቆመ ይጠባበቃል፡ ሁል ጊዜም “ለኳስ ወርዋሪው አዘንኩለት፡” ይላል።”]

[በቀይ ካርድ መውጣት ችግር የለውም፡ ነገር ግን አስታውሱ፡ ዱላችሁን አንሱት... ? ... የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በውስጤ ነውና። እባካችሁ ደግማችሁ በሉት፡ የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በውስጤ ነው። ሁሉም ነገር ነው።]

አዎን።

[ሁሉም ነገር ነው።]

ትክክል ነው።

[ሁሉም ነገር ነው።]

ሁሉም ነገር። አሜን።

[ሃሌ ሉያ። መጨቃጨቅ እና መታገል መቼም ቢሆን ስራውን አያሳካም። በጣም ተቃርበናልና... ]

አሜን።

[... ወደ ሌላኛው ጠርዝ። ወደማንመለሰበት ደረጃ ደርሰናል። ካፒቴኑ በአውሮፕላኑ ውስጥ ተመለሱ ብሎ ሲደወል ሰንት ጊዜ ሰምቻለሁ፡ “አሁን የማንመለሰበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።”]

[ከረጅም ጊዜ በፊት ከሌላ ዓለም ድምፅ ሰማሁ የተናገረኛም እንዲህ አለኝ፡ “ልጄ፡ መመለሻ ወደሌለው ነጥብ ደርሰሃል።” ይህም ከጀመርኩበት ቦታ ይልቅ ወደ ሌላኛው ወገን ቀርቤአለሁ ማለት ነው።]

[እባካችሁ አይኖቻችሁን ጨፍኑ፡ ራሶቻችሁን ዝቅ አርጉ።]

[አቤቱ የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ጥዋት፡ ምስጋናችን ብዙ ነው እናመሰግንሃለን ይህም ከልባችን እና ከነፍሳችን ጥልቅ እንልሃለን፡ “ክርስቶስ በእኔ ውስጥ—የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ፡ በውስጤ ነው።” አቤቱ፡ ኢየሱስ ሆይ፡ የፍቅር ክንዶችህን በወንዶች እና በሴቶች ሁሉ ዙሪያ አኑር፡ እና እይታችን እና ራእዮቻችን ከዚች አለም አሳቦች ከፍ—ከፍ፡ ከፍተኛ፡ እና ከፍተኛ ይሁን፡ ይህም ክርስቶስን እናይ ዘንድ፡ ሌሎችም ክርስቶስን በእኛ ውስጥ ያዩ ዘንድ ነው። እጅህን በነዚህ ባርያዎችህ ሁሉ ላይ ትሁን... ]

ሰጠን፡ ጌታ ሆይ።

[... ዛሬ ጠዋት፡ ከዚህ ቦታ ስንወጣ ከክርስቶስ በቀር ምንም ነገር እንዳናይ እንወስናለን... ]

አሜን።

[... እርስ በእርሳችን እንቀባበላለን። ስራው እንደሆነ—ኢየሱስ ሆይ፡ ስራው እጅግ ታላቅ ስራ ነው፡ የሚታጨድ ታላቅ ምርት ደርሷል።]

አዎን፡ ጌታ ሆይ።

[አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ እርዳን... ]

አዎን፡ ጌታ ሆይ።

[... አንድ ላይ እጅ ለእጅ መያያዝ እንችል ዘንድ እርዳን... ]

ሰጠን፡ ጌታ ሆይ።

[... በመኸሩ በኩል አሳልፈን... ]

አዎን፡ ጌታ ሆይ።

[... የሚጠፋውን እና የሚሞተውን ሁሉ ማጥመድ እንድንችል እርዳን።]

አዎን፡ ጌታ ሆይ።

[እጃችሁን አንሥታችሁ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንድታወድሱ እፈልጋለሁ።]... ? ...

[እንቁም፡ እባካችሁ። እጆቻችሁን አንስታችሁ ከእኔ ጋር **እወደዋለሁ** እንዘምር። ትወዱታላችሁን? ]

አሜን።

[... ዛሬ ጠዋት? በሙሉ ልብ ትወዱታላችሁን? እጆቻችሁን አንሡ እና ዘምሩት፣ ሁላችሁም አንድ ላይ፣ **እወደዋለሁ**።]

[እወደዋለሁ፣ እወደዋለሁ]
[ቀድሞ ስለወደደኝ]
[መዳኔንም ገዛልኝ]
[በቀራንዮ ዛፍ ላይ።]

[እስቲ ተቀኙ እባካችሁ? ]

[ታውቃላችሁ፡ ባልነጀሮች አገልጋዮች ሆይ፡ በአርጀንቲና ውስጥ በአንድ ጉባኤ ውስጥ ብቻ አራት መቶ ሺ ህዝብ ተሰብስቦ ነበር፡ ህዝቡን ከጊዜ ወደ ጊዜ አይተነዋል። እና የመጀመሪያውን ከስአት በኋላ አስታውሳለሁ፣ ከአራት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች በስፓኒሽ ቋንቋ እየዘመሩ ነበር፣ እና በዜማ እንዲዘምሩ ጠየቅኳቸው፡ ከውጭ ሶስት መቶ የሚያህል ህዝብ ነበር። ከውስጥ ያሉትን ዝም እንዲሉ እና ከውጭ ያሉት ብቻ መዝሙሩን እንድያዜሙ ጠየቅናቸው። እና እነሱ እየዘመሩ፡ በድንገት አንድ ነገር ነፍሴን አጥለቀለቀ። ከውጪ የሦስት መቶ ሺህ ሰዎች የድምጽ ማሚቶ እስኪንቆረቆር ድረስ በሕይወቴ ውስጥ የክርስቶስን መገለጥ በእኔ ውስጥ ከዚህ በፊት አላውቀውም ነበር በጣም **ወደድኩት**... ? ... ዛሬ ጠዋትም ታላቅ ግርማ ሞገስ ያለው የክብር የሠራዊት ንጉሥ ነው፡ እና ይዘምሩለታል። ማንን ትወዳላችሁ? ማንን ነው የምትወዱት? ]

አዎን።

[ክርስቶስ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ።]

አዎን።

[የክብር ተስፋ። አይናችሁን ጨፍኑ፡ እጆቻችሁን አንሡ፡ እና እንደገና ዘምሩለት፡ ሁላችሁም።]

አዎን ጌታ ሆይ።

[እወደዋለሁ፣ እወደዋለሁ]
[ቀድሞ ስለወደደኝ]
[መዳኔንም ገዛልኝ]
[በቀራንዮ ዛፍ ላይ።]

[ዛሬ ጠዋት እሱን የምትወዱት ከሆናችሁ፡ እጆቻችሁን በሦስት ወይም በአራት የተለያዩ ሰዎች ላይ አድርጉ፡ ሴቶችም እንዲሁ ታደርጋላችሁ፡ እና "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እወደዋለሁ፡" በሉ። በጣም ጥሩ ነው፡ እጆቻችሁን ዘርጉት… ]

337 ይህስ ሁሉ በመላ ዓለም ሲሆን ከአየሁ፡ ከእንግዲህ፡ "ጌታ ሆይ፡ ባርያህን በስላም አሰናብተኝ" እላለሁ!

**መለኮት ሲብራራ** AMH61-0425B

(The Godhead Explained)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሚያዝያ 25፡ 1961፡ ማክሰኞ ጠዋት፡ በቺካጎ ኤሊኖስ፡ ዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ከሆሊዴይ ኢን፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org